# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 290 ሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## የግል ባለሀብቶች ለልማት በተዘጋጁ ቦታዎች ላይ መዋዕለ ነዋያቸውን እንዲያፈሱ ጥሪ ቀረበ



**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- የግል ባለሀብቶች ለልማት ዝግጁ በሆኑ ቦታዎች ላይ መዋዕለ ነዋያቸውን ማፍሰስ እንደሚጠበቅባቸው የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጥሪ አቀረቡ።

አቶ ኃይለማርያም በቅርቡ በአፋር ክልል ለም መሬት ላይ የተከሰተውን አደገኛና ተስፋፊ አረም ለማስወገድ የተጀመረውን ፕሮጀክት ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለፁት፣ በአፍሪካ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲመጣ የተሟጋችነት ወይም የጠበቃነት ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

የአየር ንብረት ለውጥ ስኬት በኢትዮጵያ ጥረት ብቻ የሚመጣ ሳይሆን በመላው አፍሪካውያንና ዓለም አቀፍ ጥረት ጭምር የሚሳካ መሆኑን አመልክተው፣ ይህን ችግር በመጠኑም ቢሆን ሊቀርፍ የሚችል ፕሮጀክት ከአውሮፓ ኅብረትና ከሌሎች አጋሮቻችን ጋር በመሆን የሥሩ አካላትን እንደ አየር ለውጥ ተሟጋችነታቸው ምስጋና አቅርበዋል።

አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬትን የሚያካልለው ፕሮጀክቱ አረሙ የወረረው የመሬት ስፋት ሲታይ አንድ አንድ የአፍሪካ አገራትን የቆዳ ስፋት የሚያክል በመሆኑ መንግሥት የማሳየት ወይም የማስጀመር ሚና ብቻ እንዳለውና ዋናው የዚህ ሥራ ባለቤት መሆን ያለበት የግል ባለሀብቱ መሆኑን ተናግረዋል።

እርሳቸው እየደገፉ ባሉት የኢስት አፍሪካን ኢንቨስትመንት ግሩፕ አድቫይዘሪ ብድር አማካኝነት ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸውን አስታውሰው፣ በቀጣይም የድርሻውን ለመወጣት በአካባቢው ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

የግሉ ዘርፍ በተለይም የሲሚንቶ ፋብሪካ ባለሀብቶች የክልሉ ማህበረሰብ ለዘመናት ሲሰቃይበት የኖረውን አደገኛ አረም ወደ ኃይል ቀይሮ በመጠቀም ረገድ ድርሻቸው የጎላ መሆኑን አመልክተዋል።

አረሙን የመንቀልና ኃይል የማመንጨት ሥራ ብቻ ሳይሆን የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ በሰፊው የእርሻ ሥራ ላይ በመሰማራትና ይህ ወራሪ አረም ዳግም ተመልሶ እንዳይበቅል የተጀመረው ፕሮጀክት እስከ መጨረሻው እስኪጠናቀቅ ድረስ ከፍተኛ ርብርብ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ የዓለም አገራት ላይ


የግል ባለሀብቶች ለልማት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ‹‹በከተማም ሆነ በገጠር የሰላም ዘመቻ መታወጅ አለበት››

ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ
የቀድሞ ጦር ሰራዊት አባል

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- በከተማም ሆነ በገጠር የሰላም ዘመቻ መታወጅ እንዳለበት ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ ተናገሩ። የአገሪቷን ሰላም ለማረጋገጥ የሰውን ነፍስ በሚያጠፉ ሽፍቶች ላይ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባም አስገንዝበዋል።


‹‹በከተማም ሆነ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## «የልማት ድርጅቶች በኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስር ሆኑ ማለት ወደግል ይዛወራሉ ማለት አይደለም»

- አቶ ግርማ ዋቄ
የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ



ፎቶ ዳኜ አበራ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስር ሆኑ ማለት ወደግል ኢንቨስትመንት ይዛወራሉ ማለት አይደለም ሲሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ግርማ ዋቄ አስታወቁ።

አቶ ግርማ ዋቄ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ 27 የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በአንድ ሆልዲንግ ስር መሆናቸው ወደግል ሊዛወሩ ነው ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል።

27ቱ የልማት ድርጅቶቹ ይጠናከራሉ፤ በመልካም የአሠራር ሂደት አንዱ ሌላውን ይረዳል የሚል እንጂ፤ ድርጅቶቹ ወደግል ይዛወራሉ የሚል ሃሳብ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና አላማ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል ብለዋል።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶቹ በአንድ ሆልዲንግ ስር በበላይነት መመራታቸው አስተዳደራዊ ጉዳዮቻቸውን ለማጠናከር፣ ኢንቨስትመንታቸውን ለማሳደግና ተቋማቱን በጋራ ለማሳደግ


«የልማት ድርጅቶች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ በቀለ አንበሳ

## ባለፈው ዓመት ከተተከሉ ችግኞች 74 ነጥብ 6 በመቶዎቹ መጽደቃቸውን የቤኒሻንጉል ክልል አስታወቀ

- በዘንድሮው የአረንጓዴ ልማት አሻራ በክልሉ 44 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ችግኝ ይተከላል


ገጽ 4








አሸባሪው ሸኔ፡- የሕወሓት ጽንስ

ገጽ 7

ተስፋ የተጣለበት ዳግም ፈተና እና ዝግጅቱ

ገጽ 9

# «የምገባ ማዕከላቱ የተስፋ ብርሃን ሆነውልናል»

- በማዕከላቱ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸውና ተመጋቢዎች

ሙሳ ሙሐመድ

በመዲናዋ የተገነቡት የምገባ ማዕከላት ለሰው ልጆች የተስፋ ብርሃን ማሳያና ሰው ለሰው የመኖሩ መርህ የሚታይባቸው ናቸው ሲሉ የሥራ እድል የተፈጠረላቸውና ተመጋቢ ዜጎች ለአዲስ ዘመን ተናግረዋል።

በማዕከላቱ የሥራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል ምንም ዓይነት ሥራ ያልነበራቸው ወይዘሮ ሰሚራ ሀሰን አንዷ ናቸው። ወይዘሮዋ ባህር ማዶ በመሄድ ዓመታትን ሰርተውና ሀብት ንብረት አፍርተው፣ ለመኖር ቢታትሩም ይህ ሳይሳካ ቀርቶ ለሥራ አጥነት ተጋልጠው ያለቤት ቀርተውም እንደነበር ይናገራሉ።

ይሁንና አሁን ላይ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ዘጠኝ የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል በአስተባባሪነት ሥራ አግኝተው እየሠሩና ከራሳቸውም አልፈው ወገናቸውን በመርዳት ላይ በመሆናቸው ደስተኛ መሆናቸውን ይናገራሉ።

በዚህም ለራሳቸው ሥራ ከማግኘታቸውም በላይ እርሳቸው ያለፉበት ዕጣ ገጥሟቸውና አጋዥ አጥተው፣ ጎዳና ላይ ወድቀው ያሉትንና ያገኙትን በልተው የሚያድሩ ዜጎችን የችግርና የመከራ ልክ ያየሁበት ማዕከል ነው ሲሉም ይገልጻሉ።

ሥራው እንኳን ደመወዝ ተከፍሎ በነፃም ለነፍስ የሚሠራ ነው የሚሉት ወይዘሮዋ የሰውን ችግር፣ ሮሮ፣ ብሶት፣ ሰቆቃና ህመም መካፈልና በመጠገን ማከም ትልቅ የህሊና ርካታ እንዳለው ያወሳሉ።

በእስካሁን ዕድሜዬ ታምሜና ተጎድቼ አውቃለሁ፣ ከፈጣሪ በታች የሰዎችን ድጋፍና ርዳታ ተመኝቼም አጥቼና አግኝቼ አውቃለሁ ይላሉ።

መቸገር፣ ማጣት፣ ከሰዎች መከጀል ምን እንደሆነም ከእኔ በላይ በምድር ላይ ያየው የለም ብል ማጋነን አይሆንብኝም የሚሉት ወይዘሮ ሰሚራ የተቸገሩ ሰዎች በማዕከሉ በምግብና ሌሎች ጉዳዮች ተረድተው የተሻለ ሰው ሲሆኑና ሌላውን መርዳትና አገርን ማገልገል ሲችሉ ማየትን የመሰለ



ወይዘሮ ሰሚራ ሀሰን



አቶ አብርሃም ምስክር



ወይዘሮ አልማዝ ምህረቱ

ደስታ የትምና በምንም አይገኝም ሲሉም ያክላሉ። የራባቸው በልተውና አገልጋዮችንና አሠራሩን አመስግነው ሲሄዱ ማየት ለብቻው ሌላ ደስታን ይሰጣልም ሲሉ ያክላሉ።

ሥራ ከማግኘቴ ይልቅ የሰዎች ችግርና ስቃይ ሲቃለል ማየቴና መርዳቴ ደስተኛ አድርጎኛል የሚሉት ወይዘሮ ሰሚራ፣ የምገባ ማዕከሉን ሀሳብ የጠነሰሱት አካላት ለአገርና ለወገን መኖር ምን እንደሆነ በትክክል አሳይተዋልና ሊበረታቱና ሊመሰገኑ ይገባል ሲሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በማዕከላቱ ውስጥ ራበኝ ብሎ የመጣ ዜጋ ተመግቦ መሄድ በመቻሉም ማህበራዊ ሚዛንን፣ ፍትህንና ልማትን በማስጠበቅ ሰፊ ፋይዳ አለው የሚሉት ወይዘሮ ሰሚራ፣ ኢትዮጵያዊ ማህበራዊ መስተጋብራችንንና የመረዳዳት ባህላችንን አጠናክሮልናል፤ ከማዕከሉ ተመጋቢዎች መካከል በማዕከሉ ታግዘው ለተሻለ ደረጃ የበቁና መልሰው ሌላውን እየረዱ ያሉም አሉ ሲሉ ይገልጻሉ። ለዚህም በማሳያነት በማዕከሉ ሲታገዙ የነበሩና አሁን ላይ የአገር መከላከያ አባል ሆነው እያገለገሉ ያሉትን ይጠቅሳሉ።

አቶ አብርሃም ምስክር የተባሉ ሌላኛው በማዕከሉ ተመጋቢ በ18 ዓመታቸው በኦጋዴንና ሌሎችም አካባቢዎች በአገር መከላከያ ሰራዊት አባልነት ያገለገሉና በጦርነት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ ጎዳናዎች በአካል ጉዳተኝነት በክራንች 40 ዓመት ያለአስተዋሽ እንደኖሩም ይናገራሉ።

አቶ አብርሃም ስለማዕከሉ ሲናገሩ እየሰጠን ያለው ጥቅም በአንደበቴ ተናግሬው የሚያልቅ አይደለም።ማዕከሉ በአጠቃላይ ለነፍስ ደራሽ፣ ተስፋን አዳሽ ነው በማለት ነው። በትንሹ እንኳን ለዘመን መለወጫና መሰል በዓላት ከሚሰጠን የአልባሳትና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ገላን የማጠብ፣ ጸጉራችንን ከማስተካከል በላይ የረሃብን አለንጋ እየተከላከለልን ነው፣ በሰዓታችን መጥተን በልተንና ጠግበን ወደ ማደሪያችን እናቀናለን ይላሉ።

የ61 ዓመቱ አዛውንት አቶ አብርሃም፣ ካሳለፏቸው የዕድሜያቸው ጊዜያት ሁሉ ዛሬ ላይ ረሃብተኛን አስታውሶ ረሃብን ለማስታገስ የሚሠራ መንግሥት በማየታቸው ደስተኛ እንደሆኑ ይናገራሉ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የምገባ ጥንስሱን ለማስጀመር ሲያወሩት እውነት ሁሉን አብልተው ይዘልቁታል ወይ የሚል ጥያቄ ነበረኝ፣ ይሁንና በውስን ወራት ተሳክቶ፣ ተመጋቢውም በልቶና ደስተኛ ሆኖ ሳይ ህልም ይመስለኛል፤ ማለት የምችለውም ቅዱስና የተሳካ ተግባር ነው ሲሉ አቶ አብርሃም ገልጸዋል።

ሳገኝ በልቼ ሳጣም ጦሜን አድር ነበር አሁን ግን የረሃብ ስቃዬ በማዕከሉ ተቀርፎልኛል የሚሉት ሌላኛዋ ተመጋቢ ወይዘሮ አልማዝ ምህረቱ ናቸው።ስችል ስችል ልብስ ማጠብና መሰል የቀን ሥራን እሠራለሁ።

ማዕከሉ ግን ከልመናና በጎዳና የሰው ፊት ከማየት አድኖኛል፣ ርቦኝ ጎዳና ላይ ከመወደቅም ታድጎኛል። ወገናችን ለእኛ እንደሚያስብልንም አይቼበታለሁ፣ ደስተኛም አድርጎኛል ሲሉ ሃሳባቸውን አካፍለዋል።

# ከድንበር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት ውስጣዊ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ተጠቆመ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- መንግሥት አገሪቱ የገጠማትን ዋና ዋና ችግሮች በመፍታት ትኩረቱን ወደ ድንበር ጉዳዮች ማዞር እንዳለበት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተንታኙ ገለጹ። ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር የገባችበትን የድንበር ጉዳይ ለመፍታት ብቸኛው አማራጭ ድርድር በመሆኑ ሱዳን ለመደራደር ከ2020 በፊት ወደነበረችበት ቦታ መመለስ ይኖርባታልም ብለዋል።

የውጭ ፖሊሲ ተንታኙ ዶክተር በለጠ በላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር ያላት የድንበር ሁኔታ ለረጅም ጊዜ በችግር ውስጥ ሆኖ ሲንከባለል የቆየ ነው። ችግሩ ለረጅም ጊዜ የቆየ በመሆኑ እስካሁን ድረስ የነበሩት መሪዎች መፍታት ስላልቻሉ አሁንም ለመፍታት ቀላል ይሆናል ተብሎ አይታሰብም።

በዚህ ውስጥ መሠረታዊና ውስብስብ የሆኑ ችግሮች አሉበት ያሉት ዶክተር በለጠ፤ ሱዳንም ሆነች ሱማሊያ ነፃ ከወጡ በኋላ በተለያየ ጊዜ የተደረጉ ስምምነቶችና ድርድሮች እንደነበሩ ጠቁመዋል።



ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

ዶክተር በለጠ በላቸው

እነዚህን ስምምነቶች ወደ ኋላ በመሄድ መርምሮ በውስጡ ያሉ ችግሮችን ለይቶ አውጥቶ ወደፊት ለመሄድ መሞከር ያስፈልጋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የውስጥ ችግር በገጠማት ጊዜ ሱዳኖች የሚፈልጉትን ነገር ለማሳካት ይፈልጋሉ ያሉት ተንታኙ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ አንጻራዊ የሆነ ሰላም፣ መረጋጋትና ጥንካሬ ሲኖር ጉዳዩን ወደ ውይይት የመውሰድ ዝንባሌ ይታያል ብለዋል።

እንደ ዶክተር በለጠ ገለጻ ከሆነ፤ የኢትዮጵያ መንግሥታት ጠንካራ ሲሆኑ እነዚህ መንግሥታት ጉዳዩን እንዴት እንፍታው በማለት ወደ ውይይት ይገባሉ። ኢትዮጵያ ችግር ሲገጥማት ደግሞ ለመሸራረፍና የሚፈልጉትን ነገር ለማሳካት ይሞክራሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያ በድንበር ጉዳይ ላይ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት መፍቻ መንገድ የሚሆነው የውስጥ ደህንነትን ማረጋገጥ፣ የመንግሥት መረጋጋትና የመንግሥት የበላይነትንና ውስጣዊ አንድነትን ማጠናከር ነው።

የውስጥ ጉዳያችንን ሳንፈታ የድንበር ጉዳያችንን ማስተናገድ አይቻልም ያሉት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተንታኙ፤ ይህ ሳይሆን ድርድር ይደረግ ቢባል ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ያጋልጣል። ድርድሮች የሚመሩት በማዕከላዊ መንግሥት በመሆኑ ማዕከላዊ መንግሥት አገሪቱ የገጠማትን ዋና ዋና ችግሮች በመፍታት ትኩረቱን ወደ ድንበር ጉዳዮች ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል።

የድንበር ጉዳዮች የሚፈቱት በአገራቱ መንግሥታት መካከል በሚደረግ ውይይትና ድርድር ነው። ይህ ሳይሆን የትኛውም ወገን በኃይል ቢይዝ ነገ በኃይል እንደሚነጠቅ ይታወቃል። ስለዚህ ጉዳዩን ከዓለም አቀፍ መርህ አንጻር፣ የአፍሪካ ህብረት፣ አፍሪካ አንድነት ድርጅት መርሆችን ተግባራዊ በማድረግ ጉዳዩን በንግግርና በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ለሁሉም የሚጠቅም ነው ሲሉ ዶክተር በለጠ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያና የሱዳንን ደንበር ጨምሮ አፍሪካ ቀንድ በደንበር ዙሪያ ብዙ ውስብስብ ጉዳዮች ያሉ በመሆናቸው በሕግና በፖለቲካ ውሳኔ ብቻ ሊፈቱ የሚችሉ እንዳልሆኑ የጠቆሙት ዶክተር በለጠ፣ የማህበረሰብ ጉዳዮችና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጉዳዮች መታየት አለባቸው። ስለዚህ እነዚህን ጉዳዮች ባስጠበቀ መልኩ ሊፈታ የሚችው አገራቱ ቁጭ ብለው መነጋገር ሲችሉ ነው ብለዋል።

ብቸኛው አማራጭ ሁለቱም ወገኖች ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ ብቻ መሆኑን ያወሱት የፖሊሲ ተንታኙ፤ ሱዳን ከ2020 በፊት ወደነበረችበት ቦታ መመለስ አለባት። ይህን ሀሳብ ሱዳኖችም መቀበል አለባቸው። መሬቱ ለሱዳንም ይሁን ለኢትዮጵያ ይወሰን መጀመሪያ ሱዳን በኃይል ከያዘችው ቦታ በመውጣት ለውይይትና ለድርድር ዝግጁ መሆን እንዳለባት ዶክተር በለጠ በላቸው ተናግረዋል።

ዜና

# ሕወሓትና ሸኔ በአማራና በኦሮሞ ሕዝብ መካከል ተከታታይ ግጭት እንዲፈጠር ሲሠሩ መቆየታቸው ጥናት አመለከተ

**ሞገስ ጸጋዬ**

ደብረ ብርሃን፡- ከአገራዊ ለውጡ በኋላ በአማራና በኦሮሞ ማኅበረሰብ መካከል የነበሩ ማህበራዊ ግጭቶች ተከታታይነት ወዳለው ጥቃት እንዲሸጋገር የሕወሓትና ሸኔ ቡድኖች ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የፌዴራሊዝምና አስተዳደር መምህር አስታወቁ።

በሁለቱ ሕዝቦች መካከል ስላለው ማህበራዊ መስተጋብር ጥናት ያደረጉት ዶክተር ታምራት ቸሩ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከአገራዊ ለውጡ በፊት በአማራና በኦሮሞ ማህበረሰብ መካከል በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና በመሬት ግጦሽና በማህበራዊ ግንኙነቶች አልፎ አልፎ የሚፈጠሩ ግጭቶች ነበሩ። ነገር ግን ከግጭትነት የዘለለ ችግር እንዳልነበረውና በባህሪውም ከወቅታዊነት የማያልፍ እንደነበር ገልጸዋል።

እንደ ዶክተሩ ገለጻ፤ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ ቀጠናውን እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም በሁለቱ ትላልቅ ሕዝቦች መካከል ቀደም ሲል የነበረው የማህበራዊ ግንኙነት ግጭት ቅርጹን እንዲቀይር በማድረግ ብዙ አካላት ተሳትፈዋል። በዋናነት ግን የሕወሓትና ሸኔ ሚና የጎላ ነበር ብለዋል።

እንዲሁም ከአካባቢ አልፎ በሁለቱ ሰፊና ትላልቅ ክልሎች መንግሥታት መካከል ቁርሾና መናቆር እንዲኖር ለማድረግ የሕወሓትና የሕወሓትን ተልዕኮ ተቀብሎ የሚያስፈጽመው ሸኔ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደተሳተፉ ኅብረተሰቡ ለጥናቱ በሰጡት መረጃ ማረጋገጥ መቻሉን አብራርተዋል።

ቀደም ሲል የነበረውን ግጭት ቅርጽን ለውጦ ከግጭትነት አልፎ ወደ ተከታታይነት ጥቃት እንዲሸጋገር በማድረግ የበርካታ ንጹሐን ዜጎች ሕይወት አልፏል ያሉት ጥናት አቅራቢው፤ ይህም በንብረት ላይ ውድመትና በሁለቱም ኅብረተሰብ ዘንድ ፍርሃት እንዲነግስ ማድረጉንም ገልጸዋል።

የአማራና ኦሮሞ ማህበረሰብ ለዘመናት ጠንካራ የሆነ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መስተጋብርና ትስስር ያላቸው ናቸው ያሉት ዶክተር ታምራት፤ ሕዝብ እንደ ሕዝብ አንዱ በአንዱ ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው አይንቀሳቀሱም። ነገር ግን የራሳቸውን ፍላጎት በሕዝብ ላይ በመጫን በኅብረተሰብ መካከል ያለ መልካም ግንኙነት እንዲሻክር፤ ከዚያ አልፎ በአገር ደረጃ ሰላም እንዳይኖር በማድረግ ረገድ የሕወሓትና የሸኔ ቡድን አሉታዊ ሚናን ተጫውተዋል ብለዋል።

አገራዊ ለውጡ መርህ አልባና የተለያዩ ፍላጎቶች ያለ ሕግ እንዲመሩና የራስን ፍላጎት በሕዝብ ላይ ለመጫን ሁከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር የሕወሓትና የሸኔ ቡድኖች ዋና ተዋናይ ነበሩ ያሉት ዶክተር ታምራት፤ እንዲሁም ሕገወጥ መሣሪያና የሰዎች አዘዋዋሪ አካላት ምቹ ሁኔታን በመጠቀም ፍላጎታቸውን ኢ ሰላማዊ በሆነ እንቅስቃሴ ለመተግበር የሚያደርጉት ሚና አለ ብለዋል።

በየአካባቢው የሚገኙ የመንግሥት መዋቅር ለችግሩ የመፍትሄ አካል ከመሆን ይልቅ እንወክለዋለን ለሚሉት ማኅበረሰብ ወገንተኛ መስሎ በመታየት ችግሩ እንዲባባስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዳደረጉም ዶክተር ታምራት አብራርተዋል።



ዶክተር ታምራት ቸሩ



የሀምሳ አለቃ ገነት ብርሃኑ



መምህር ቦጋለ ኦብሳ



የሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ



መቶ አለቃ ተክሉ ወልዴ

# መገፋት ያላደበዘዘው የአገር ፍቅር ስሜት

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ እንዲከበርና አገረ መንግሥቷ እንዲጸና ዕልፎች ዋጋ ከፍለዋል። በርካቶች ግን ‹ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ› እንዲሉ ለከፈሉት ዋጋ ሽልማት ሳይሆን እስራት ከፍ ሲልም ሞት ተከፍሏቸዋል።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት ደግሞ የኢትዮጵያ የቀድሞው ሠራዊት አባላት ናቸው። ሠራዊቱ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር ተራራ ሲወጣ አቀበት ሲወርድ ዘመናትን አሳልፏል። የደርግ መንግሥት ተወግዶ ሕወሓት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት አገሪቱን ሲረከብ ግን የሠራዊቱ ዕጣፈንታ መበተን ሆነ።

ይሁንና በወቅቱ አታስፈልጉም ቢባሉም እነሱ ግን ልባቸው በአገር ፍቅር የጸና እንደነበር ይናገራሉ። ከእነዚህ ጀግኖች መካከል በቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ በአመራርነት ጭምር ለበርካታ ዓመታት አገራቸውን በታማኝነት ያገለገሉት የሃምሳ አለቃ ገነት ብርሃኑ አንዷ ናቸው።

ኢህአዴግ ስልጣነ መንበሩን ሲቆጣጠር ሠራዊቱን በመበተኑ ከሚወዱት ሙያ በመነጠላቸው ለዓመታት ኀዘንና ልብ ስብራት ውስጥ ሆነው መቆየታቸውን የሃምሳ አለቃ ገነት ብርሃኑ ይናገራሉ።

ሠራዊቱ ለአገር ለከፈለው ዋጋ ምስጋና ሳይሆን ወቀሳና እንግልት ተከፍሎታል የሚሉት ሃምሳ አለቃ ገነት፤ እኛ በየበረሃው የተንከራተትነውና የተዋጋነው ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሆኖ ሳለ «የደርግ ሠራዊት» የሚል የዳቦ ስም በመስጠት ሠራዊቱ አንገቱን እንዲደፋና እንዲገለል ተደርጓል ይላሉ።

ሠራዊቱ በመበተኑ ኑሮን ለማሸነፍ ብዙ ውጣ ውረድ ቢያሳልፍም፣ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራና አፋር ክልሎች ላይ የፈጸመውን ወረራ ተከትሎ አገራዊ ጥሪ ሲቀርብ የአማራ ልዩ ኃይልን ተቀላቅለው አገራቸውን በሙያቸው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

የአገር ሉዓላዊነትና አንድነትን ማስጠበቅ ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ ስላልሆነ ለሠራዊቱ ጥሪ ሲቀርብ ዕድሜያቸውን ቀንሰው የገቡ ሰዎች ሁሉ መኖራቸውን የሚያስታውሱት ሃምሳ ዓለቃዋ፤ መንግሥትም የቀድሞውን ሠራዊት መለስ ብሎ ሊመለከተው ይገባል ብለዋል።

አገራቸውን ለበርካታ ዓመታት በወታደርነት ያገለገሉት መምህር ቦጋለ ኦብሳ በበኩላቸው፤ ሠራዊቱ ሲበተን ወደ ሱዳን ተሰደው ከቆዩ በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው በመምህርነት አገራቸውን እያገለገሉ ይገኛሉ።

የቀድሞው ሠራዊት ያለምንም መከፋፈል አገሩን ሲያገለግል መኖሩን አስታውሰው፤ ሕወሓት ለ27 ዓመታት የዘራው የመለያየት ዘር ፍሬ አፍርቶ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ሁኔታ ውስብስብና ዜጎች እርስ በርስ የማይተማመኑበት ሁኔታ ላይ እንዲደርሱ ማድረጉን ይጠቅሳሉ።

ችግሩን ለመቀልበስ ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውን አጠናክረው ኢትዮጵያ እንደአገር እንድትቀጥል ያለመታከት እንዲሠሩ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት የድጋፍና ልማት ማህበር ፕሬዚዳንት የሃምሳ አለቃ ብርሃኑ አማረ እንደሚሉት ደግሞ፤ የማህበሩ አባላት የአገር ጉዳይ ሁሌም ያሳስባቸዋል።

ከዚህ ቀደም የነበረው መገፋትና መገለል ከአገር ስለማይበልጥ ኢትዮጵያ አገልግሎታችንን በፈለገች ጊዜ ሁሉ ግንባር በመዝመትም ሆነ በማሰልጠኛ ጣቢያዎች በመገኘት ልምዳችንን ያለ ስስት አካፍለናል። ወደፊትም ለኢትዮጵያ ህልውና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከፊት እንሰለፋለን ሲሉ ቁርጠኝነታቸውን ይገልጻሉ።

ማህበሩ በአቅሙ ልክ ለአገር ማበርከት የሚችለውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት መንግሥት ለሠራዊቱ በተናጠልም ሆነ እንደማህበር አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ነው የሚያሳስቡት።

በቀድሞው የኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ አገራቸውን በታንከኝት ያገለገሉት መቶ አለቃ ተክሉ ወልዴ በበኩላቸው፤ በሙያዬ አገልግዬ በኋላ አታስፈልግም ብባልም አሁንም የአገር ፍቅር ውስጤ እንዳለ ነው ይላሉ።

በወቅቱ በሙያቸው ታሪክ መስራታቸውን በማስታወስ፤ በኢትዮ- ሶማሌ ጦርነት ወቅት እየተከተላቸው የነበረውን የጠላት ታንክ አባረው በመግጨት ታንኩ እንዲቆም ካደረጉ በኋላ በደፈጣ ጥቃት ሊሰነዝርባቸው የነበረውን ምድብተኛ ጦር በቦምብ በመጨረስ ታላቅ ጀብዱ መፈጸማቸውን ይናገራሉ።

በኋላ ግን እንደማይጠቅም ተበተንን ሲሉ በቁጭት ይናገራሉ። ይሁንና የቀድሞው ሠራዊት አገሩን ከቤተሰቡ በላይ ይወዳል፤ እኔም የኢትዮጵያ ሁኔታ ሁሌም እንቅልፍ ይነሳኛል ሲሉ ስሜታቸውን ይገልጻሉ።

በሕልውና ዘመቻው ወቅት የቀረበውን ጥሪ ተከትሎ ድጋሚ የመዝመት ፍላጎት ቢኖረኝም በዕድሜ መግፋት የተነሳ ሊሳካልኝ አልቻለም፤ ይሁንና ሁሉም ነገር ከአገር በታች ስለሆነ የአገርን ሠላም ለማስከበር በዚህ ዕድሜዬም ቢሆን ዝግጁ ነኝ ይላሉ።

የቀድሞው ሠራዊት አባላቱ ለትውልዱ ቋንቋንና ባህላችሁን ለማዳበር፣ ተምራችሁ ለመለወጥ፣ ወልዳችሁ ለመሳምና በአጠቃላይም የምታልሙትን ሁሉ ለማሳካት አገር ያስፈልጋችኋልና አገራችሁን ጠብቁ የሚል አባታዊ ምክር አስተላልፈዋል።

ስለሆነም ከመለያየት ይልቅ መሰባሰብን ከመገፋፋት ይልቅ መተጋገዝን፣ ከእኔነት ይልቅ እኛነትን ከልዩነት ይልቅ አብሮነትን አስቀድማችሁ በብዙ ዋጋ የተረከባችኋትን አገር ከነሙሉ ክብሯና ነፃነቷ ለቀጣዩ ትውልድ አስረክቡ ሲሉ የሠራዊቱ አባላት ምክራቸውን ለግሰዋል።



# አምባሳደር ዶክተር ኢንጂነር ስለሺ ከአሜሪካ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ከተውጣጡ 25 ፕሮፌሰሮች ጋር ተወያዩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ዶክተር ኢንጂነር ስለሺ በቀለ በአሜሪካ ከሚገኙ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ከተውጣጡ 25 ፕሮፌሰሮች ጋር ውይይት ማካሄዳቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ።

አምባሳደር ስለሺ በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ ጉዳዮች ላይ ጠቅለል ያለ ውይይት ከምሁራኑ ጋር ማካሄዳቸውን የጠቆሙ ሲሆን፣ በተለይም በተፈጥሮ አደጋዎች፣ በግጭቶች፣ በምግብ ዕጥረት እንዲሁም በፍልሰት ላይ ሃሳቦችን መለዋወጣቸውን አንስተዋል።

ችግሮቹ ሕዝብ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖ ለመቀነስ እና ዕልባት ለመስጠት የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችም መነሳታቸውን አምባሳደር ዶክተር ስለሺ ጠቅሰዋል።

በአሜሪካ የሚገኘው የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበረሰብም በአገራቱ መካከል የቆየውን የሁለትዮሽ ግንኙነት በማጠናከር ረገድ እየተወጣ ያለውን ሚናም አስረድተዋል።

ምሁራኑ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የአፍሮ-አሜሪካውያንን ስኬት ያነሱ ሲሆን ፣ በአሜሪካ ከነሱ በሚጠበቅ ማናቸውም ነገር የበኩላቸውን ለመወጣት ዝግጁ መሆናቸውንም አስታውቀዋል።

አምባሳደር ዶክተር ስለሺ፣ ምሁራኑ ስለ ኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ስለሚኖሩ የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎች ለማወቅ ያላቸውን ጉጉት አድንቀው ይህን መሰል ግንኙነት የአገራቱን ወዳጅነት እና ትብብር ያጠናክራል ማለታቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

በኢትዮጵያ እና በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የሁለትዮሽ መርሃ-ግብሮች ፣የጋራ የምርምር ሥራዎች እና በተማሪዎች መካከል የሚኖሩ የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ ጠቀሜታቸው የጎላ መሆኑንም አስምረውበታል።

# ባለፈው ዓመት ከተተከሉ ችግኞች 74 ነጥብ 6 በመቶዎቹ መጽደቃቸውን የቤኒሻንጉል ክልል አስታወቀ

## - በዘንድሮው የአረንጓዴ ልማት አሻራ በክልሉ 44 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ችግኝ ይተከላል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በባለፈው ዓመት ከተተከሉ 31 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ችግኞች መካከል 74 ነጥብ ስድስት በመቶዎቹ መፅደቃቸውን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ። በዘንድሮው የአረንጓዴ ልማት አሻራ በክልሉ 44 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ ተገልጿል።

የክልሉ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በቀለ አንበሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ባለፈው ዓመት ከተተከሉ ችግኞች ሦስት አራተኛው ጸድቀዋል። ይህንን ውጤት በቀጣይ ጊዜያት አጠናክሮ ለመቀጠል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በክልሉ አረንጓዴ ልማት አሻራ መርሃ ግብር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ሲሠራበት መቆየቱን አስታውሰው፤ በየዓመቱ የሚተከሉ ችግኞች ቁጥርም ሆነ የፅድቀት መጠኑ እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመዋል።

ለአብነት በ2011 ዓ.ም ከ43 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ችግኝ ከተተከለ በኋላ 68 በመቶዎቹ ችግኞች መፅደቃቸውን ገልጸዋል። ይህ የጽድቀት መጠን አሁን ላይ 74 ነጥብ ስድስት በመቶ መድረሱ የሚበረታታ መሆኑን ተናግረዋል።

የተተከሉ ችግኞችን ከመንከባከብ አንፃር ክልሉ በትኩረት የሚሠራበት መሆኑንና በዓመት ሁለት ጊዜ የተተከሉትን ችግኞች የመቁጠር ሥራ እንደሚከናወንም ገልጸዋል።


ባለፈው ዓመት የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ቀደም ብለው የተተከሉ ችግኞች ተስፋ ሰጪ ደረጃ ላይ መሆናቸውን አቶ በቀለ አስታውቀዋል።

ኅብረተሰቡም በአፈርና ውሃ ጥበቃ መርሃ ግብሮች ላይ ከተከናወኑ ተግባራት ላይ ተጠቃሚ እየሆነ በመምጣቱ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ላይ በንቂስ እየተሳተፈ ይገኛል ብለዋል፡፡

ማህበረሰቡም ከመትከል ባሻገር የተተከሉት ችግኞች ከእንስሳትና ሰው ንክኪ ነፃ በማድረግ ረገድ ሚናው እየጎላ መምጣቱን ምክትል ኃላፊው ጠቁመዋል።

በመሆኑም በተያዘው ዓመት በክልሉ በሦስት ዞኖችና አንድ ልዩ ወረዳ 44 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ችግኝ ይተከላል። ለዚህም በስድስት ሺህ 652 ሄክታር መሬት ላይ ሁለት ሚሊዮን በላይ የችግኝ ጉድጓድ መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

እንደ አቶ በቀለ ገለፃ፤ ከሰኔ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በክልል ደረጃ የችግኝ ተከላ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር በይፋ ይጀመራል። ለዚህም ከከፍተኛ አመራር፣ በግብርና ባለሙያ ደረጃና በኅብረተሰቡ ዘንድ ድረስ አስፈላጊው ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡



አቶ በቀለ አንበሳ

የችግኝ ተከላ መርሃ ግብሮቹ በመደበኛና በአንድ ጅምበር የሚተከሉ ችግኞች ተብለው የሚካሄዱ ዘመቻዎች ሲሆኑ፤ እንደ ክልሉ አፈርና የአየር ሁኔታዎች መሠረት ለደንና ኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚውሉ እንዲሁም ለአትክልትና ፍራፍሬዎች የሚውሉ ችግኞች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

ክልሉ ታላቁ የህዳሴው ግድብ የሚገኝበት ስፍራ እንደመሆኑ መጠን ግድቡ በደለል እንዳይሞላና አካባቢው በደን እንዲሸፈን በተለየ መልኩ ኃላፊነት እንዳለው የጠቆሙት አቶ በቀለ፤ ግድቡን ታሳቢ ያደረገ የአፈርና አካባቢ ጥበቃ ሥራ በስፋት እንደሚከናወን አስረድተዋል።

የክልሉ መንግሥትም የአካባቢን ብዝሃ ሕይወት የሚጠብቅ፣ ለማህበረሰቡ ዘላቂ ጥቅም የሚውሉ እንዲሁም ለደን ልማት የሚሆኑ ተክሎች ላይ አተኩሮ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በተለይም ክልሉ በቀርከሃና በማንጎ ልማት የሚታወቅ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላቸውንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርት የሚሰጡ ችግኞችን በብዛት እንዲለሙ ትኩረት መሰጠቱን አቶ በቀለ ገልጸዋል።

# «የልማት ድርጅቶች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከመፈለግ የመጣ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ግርማ ዋቄ ገለጻ፤ የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ አሠራር በሌሎች አገራትም ተሞክሮ ውጤት ያመጣ አሠራር ነው። በሲንጋፖር ኢኮኖሚያቸው ከመሠረቱም ሲያድግ የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ አካሄድን ጥቅም ላይ አውለው ከተሞቻቸውን አሳድገዋል።

በዱባይም እንደታየው «ዱባይ ኢንክ» የተሰኘ የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ካቋቋሙ በኋላ ሰፊ የልማት ሥራዎች አከናውነዋል። ያደጉ አገራት በዚህ አካሄድ ተቋማቶቻቸውን አጠናክረው የተሻለ ኢኮኖሚ ገንብተዋል ሲሉ አቶ ግርማ ገልጸዋል።

በመሆኑም በኢትዮጵያም የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ሥራ ቢዘገይም በቅርቡ ተቋቁሞ ወደሥራ መግባቱ ለአገር የሚበጅ አካሄድ መሆኑን ተናግረዋል።

ሰሞኑንም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ተቋምን አላማ፣ የልማት ድርጅቶቹ አሠራርና አጠቃላይ የግንኙነት መስመሩን በተመለከተ ሰፊ ውይይት መካሄዱን የጠቆሙት አቶ ግርማ፤ ይህም አሠራርና ሥርዓቱን ለበርካቶች ግልጽ ያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያም የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ሲቋቋም የእያንዳንዱን የልማት ድርጅት ቦርድ ተክቶ የሚሠራ አለመሆኑን መረዳት ይገባል ብለዋል።

የ27ቱንም የልማት ድርጅቶች ቦርድ ቢኖራቸውም የኢትዮጵያም የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የበላይ ሆኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ኢንቨስትመንት እንዴት ይሻሻላል የሚለው ላይ በትኩረት እንደሚሠራ ግልጽ መደረጉን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያም የኢንቨስትመንት ሆልዲንግ በተለይም የልማት ድርጅቶቹን የካፒታል አጠቃቀም፣ የሥራ ክንውንና አስተዳደር ሥርዓት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን በማሳደግ ረገድ ከየተቋማቱ ኃላፊዎችና የቦርድ አመራሮች ጋር በቅንጅት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

እያንዳንዱ የልማት ድርጅት በሚያቀርበው ዕቅድና አፈጻጸም መሠረት ይበልጥ እንዲጠናከሩ አሊያም ወደኋላ ከቀሩ እንዴት መሻሻል አለባቸው የሚለው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ይመክርበታል። ይህ አካሄድ እንደአገር በኢንቨስትመንት ዘርፍ ያለውን ክንውን ለማጠናከር ይረዳል ብለዋል። በዚህ አግባብ ከታየ ለአብነት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ የታየው ለውጥ በስኳር ፋብሪካዎች አካባቢ ከሌለ የአየር መንገዱን አሰራር እንዴት ወደስኳር ፋብሪካዎች ወስጄ ጠንካራ ኢኮኖሚ እገነባለሁ የሚለው ላይ ይመከራል፤ ይተገበራል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ግርማ ዋቄ ከሆነ፤ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስር ያሉ 27 የልማት ድርጅቶች ተደጋግፈው እንዲያድረጉ ጥረት ይደረጋል። ይህ አሠራር ለአገርም ሆነ ለየተቋማቱም የሚመከር አሠራር በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በ100 ቢሊዮን ብር የተፈቀደ ካፒታል የተቋቋመ ባለ ብዙ ሥራ ተቋም ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተቋሙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ናቸው።

# የግል ባለሀብቶች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በመንቀሳቀስ ከከፍተኛ ባለሀብቶች ጋር የመገናኘት ዕድል ያላቸው መሆኑን ገልፀው፣ ይህን ዕድል በመጠቀም ትላልቅ ባለሀብቶችን በማምጣትና አካባቢውን እንዲያለሙ የማድረግ ተግባራቸውን በእርሳቸው በኩል እንደሚወጡ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ኃይለማርያም ገለፃ መንግሥት በሁሉም የልማት ዘርፎች ላይ የሚሰማራ አካል አይደለም። በቅድሚያ አገራዊ ባለሀብቶች ዓይናቸውን በመክፈት ለልማት ዝግጁ የሆኑ ቦታዎችን በማልማት የአገራዊ ልማት ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።

በሌላ በኩል መንግሥት ዓለም አቀፍ የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ልማት እንዲገቡና ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግም ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል።

«የአካባቢው ማኅበረሰብ ከዚህ ፕሮጀክት የሚገባውን ጥቅም እንዲያገኝ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም የግል ባለሀብቶች አስተዋፅኦ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እኔም የሚጠበቅብኝን ኃላፊነት እወጣለሁ» ብለዋል።

# ‹‹በከተማም ሆነ በገጠር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ በተለይ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ መንግሥት ለሕወሓትም ሆነ ለሸኔ የሠላም ጥሪ አቅርቧል። ሆኖም ሁለቱም አልተቀበሉትም። አሁንም ግን እታች ድረስ በመውረድ ለሁሉም በሚገባው ቋንቋ ስለሰላም ሊነገረው ይገባል ብለዋል።

እንደ ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ገለጻ፤ ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት የሽብር ቡድኑን ሕወሓት አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ ከአማራና ከአፋር ክልሎች አስወጥቷል። ነገር ግን ቡድኑ አሁንም የጦርነት ዝግጅት እያደረገ መሆኑ እየተነገረ ነው። ሆኖም ጦርነት አይጠቅምም። የመጨረሻው ውጤት ጥፋት ብቻ በመሆኑ፤ የሚጠቅመው በሰላማዊ መንገድ ችግርን መፍታት ነው።

ኢትዮጵያ መልካም ባህል አላት ያሉት ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን፤ የሃይማኖት አባቶችን፤ አባገዳዎችን እና ሽማግሌዎችን በመያዝ በየጎሳው ማስተማር የግድ ነው፤ በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለውን ሰው ስለሰላም በተደጋጋሚ በማስተማር ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ ብለዋል።

ሰውን ለመግደል መነሳት፤ እጅግ የሚያሳዝን የኋላቀርነት ተግባር ነው ያሉት ጄኔራሉ፤ በወለጋ የተፈፀመውም ተግባር አሳፋሪ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ገለፃ፤ አሁን የአማራም ሆነ የኦሮሞ አምባገነን መኖር የለበትም። ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ሁሉም እኩል እንደሆነ ማሳየት አለበት። አሁን በኢትዮጵያ እየተፈፀመ ያለው ጥፋት መንግሥትን ከመናቅ የመነጨ በመሆኑ፤ ይህንን ጥፋት ለማስቆም ስለሰላም ማወጅ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኞች ላይ አስተማሪ እርምጃ መውሰድም የግድ እንደሆነ ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ተናግረዋል።

የሚታየው ጥፋት በዚህ ከቀጠለ አስቸጋሪ ነው ያሉት ጄኔራሉ፤ አሁንም ጥፋት እንደአሸን እየፈላ ነው፤ መንግሥት በየኬላው ወታደር ማቆም አይችልም፤ ነገር ግን በምዕራብ ኦሮሚያ በጊምቢ ወረዳ፣ በጋምቤላም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ጥፋት የፈፀሙ ሽፍቶች ላይ ሕግን ተከትሎ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ ውጤት ማምጣት ይቻላል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገርን እንደ ሀገር የማስቀጠል ፈተናን አሸንፎ ለመውጣት!

ብዙዎች ከለውጥ ማግስት ጀምሮ በዚህች ሀገር እየሆነ ስላለው ነገር ያላቸው ግንዛቤ የተሟላና በተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ አይደለም። ከዚህ ይልቅ በጥላቻ ድምፆች ፣ በተዛቡ አሉባልታዎችና በፌስቡክ የተበከሉ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱና ለእነዚሁ ሃሳቦች የተገዙ ናቸው። ከዚህ የተነሳም ዜጎች ስለሀገራቸው ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘትም ሆነ እውነተኛውን ሀገራዊ እውነታ ለመረዳት እያጋጠማቸው ያለው ተግዳሮት ከፍ ያለ ነው።

በተለይም አሁን በሀገሪቱ ስላለውና መንግሥትና ሕዝብን እየተፈታተነ ስለሚገኘው ኢንፍሌሽን /የገንዘብ የመግዛት አቅም መውረድና ይህንነው ተከትሎ እየተፈጠረ ስላለው የኑሮ ውድነት በሕዝባችን ውስጥ ያለው የግንዛቤ ክፍተት ችግሩን ወደ አንድ አካል (ወደ መንግሥት) ከመቀሰር ያለፈ አለመሆኑ ችግሩን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችን ፈታኝ አድርጓቸዋል ።

የለውጥ ኃይሉ ወደ ስልጣን ከመጣበት ቀን ጀምሮ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን እና የእነርሱ ተላላኪ የሆኑ የውስጥ ባንዳዎች ሀገርን እንደ ሀገር በማፍረስ ሕዝባችንን ለመበተን የሄዱበት መንገድ ከፍ ካለ መስዋዕትነት ባለፈ ብዙ ሀብት ጠይቆናል፤ በተለይም የሀገር ምሰሶ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊት ሀገራዊ ኃይል አድርጎ ለመገንባት የከፈልነው ዋጋ ብቻ እንመልከት።

በዘመነ ሕወሓት ሀገራዊ ቁመና ያልነበረው ይህ ተቋም አሸባሪው ሕወሓት በፈጠረው የእብሪት ጦርነትና ጦርነቱን ለመቀልበስ በተካሄደው እልህ አስጨራሽ ትግል ያለውንም አቅም እንዲያጣ ሆኗል። በዚህም መንግስት ለተቋሙ ቅድሚያ ሰጥቶ ለመንቀሳቀስ ፤ ብዙ ሀብትም ለማፍሰስ ተገድዷል።

መንግሥት ባለፉት አራት ዓመታት በአሸባሪው ሕወሓት የስልጣን ዘመን ጀምሮ እየፈረሰች የነበረችውንና በራሱ በቡድኑ የመፍረስ አደጋ ውስጥ ገብታ የነበረችን ሀገር ከመፍረስ ታድጎ ፤ በሁለት እግሯ እንድትቆም እየሠራ ነው። ይህም ሀገራችን የሶሪያ ፣ የመንና የሊቢያን እጣ ፈንታ እንዳትጋራ አድርጎታል ።

ለዚህም በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሀብት አስፈልጎናል ፤ በብዙ መስዋዕትነት የተገኘውንም ድል አስጠብቆ ለመሄድ የመከላከያ ኃይሉን ከማጠናከር አንጻርም ገና ብዙ ሀብት መፍጠርና ኢንቨስት ማድረግ ይጠይቃል። ይህን ማድረግ የየትኛውም መንግሥት ትልቁና ዋነኛው ኃላፊነት ነው።

ስለ ሀገር ከፍ ያለ ትርጉም ላለንና ሁሌም ቢሆን ስለ ሀገር መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ለሆንን ለኛ ኢትዮጵያውያን ሀገርን ከመፍረስ አደጋ ለመታደግ የከፈልነውም ሆነ ወደ ፊት ልንከፍል የምንችለው ሁለንተናዊ መስዋዕትነት አሁን ከዋጋ ንረት ጋር በተያያዘ እየከፈልነው ካለው ዋጋ ጋር የሚነፃጸር አይደለም።

በአንድም ይሁን በሌላ አሁን የተፈጠረው የኑሮ ውድነትና የኑሮ ውድነቱ የፈጠረው ፈተና ሀገርን እንደ ሀገር ለመታደግ የሄድንበት የፈተና መንገድ አካል እንጂ ተራ በሆነ የመንግሥት ግዴለሽነት የተፈጠረ አይደለም። ሀገርን በማስቀጠል ቀጣዩን ፈተና መጋፈጥ ወይስ ችላ ማለት የሚለውንም ታሳቢ ያደረገ ነው ።

ይህ ደግሞ ሀገርን ማስቀደም ስለሆነ የጤነኛ መንግሥት ባህሪ ነው። በተለይም እንደኛ ላለች ጠላቶቿ መቼም ቢሆን ተኝተው ለማያድሩላት ሀገር ፤ለሀገር ሕልውና መሠረት የሆነውን የመከላከያ ኃይል ቅድሚያ ሰጥቶ በአግባቡ ማደራጀትና አስተማማኝ ቁመና እንዲላበስ ማድረግ ለመጪው ዘመን አስተማማኝ መሠረት መጣል ነው።

ዓለም ራሷ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ባለችበት ወቅት ያጋጠመን የኑሮ ውድነት ሀገርን እንደ ሃገር የማስቀጠል ፈተና አካል እንደሆነ መረዳትና ፈተናውን አሸንፎ ለመወጣት እንደ ሕዝብ ከፍ ያለ ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅብናል። ችግሩን ወደ አንድ አካል ከመውሰድ እና ችግር ከመተንተን ወጥተን ሁላችንም የመፍትሔው አካል ልንሆንም ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# በሜጋ ፕሮጀክቶች አካባቢ አሁን የሚታየውን የፀረ ሙስና ትግል ለማስቀጠል—

**ይቤ ከደጃች ውቤ**

ኢሕአዴግ በትረ መንግሥቱን ከጨበጠ ቆየት ብሎ የፌዴራል ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተቋቋመ። ስሙም እንደሚናገረው ኮሚሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ ሙስና ለማጥፋት(ማጥፋት እንኳን አይቻልም) ሙስናን ለመከላከል ነው። ይሁን እንጂ ውጤቱ በተቃራኒው ሆኖ አረፈው።

ሙስና ለማስፋፋት የተቋቋመ እስኪመስል ድረስ ከኮሚሽኑ መቋቋም በኋላ ችግሩ በመቀነስ ፋንታ በመላ ሀገሪቱ ይባሱኑ ተንሠራፍቶ ተስተዋለ። በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፓርላማ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት ካነሱት ጉዳይ አንዱ የሌብነት/የሙስና ጉዳይ ነው። ጉዳዩ ፀሐይ የሞቀው ሐቅ በመሆኑ ብዙ ለመከራከርና ለመሟገት የሚመች አይደለም።

ፀረ ሙስና ሲጀመር እንደተቋቋም ከፍ ያለ ስልጣንና ኃላፊነት ተሠጥቶት ሥራ ቢጀምርም በኋላ ግን ስልጣንና ኃላፊነቱን በሕግ ተነጥቆ ጥርስ የሌለው አንበሳ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ተቋሙ ስሙን ታቅፎ ሙስና ሲፈጸም እያየ እንዳላየ፣ እየሰማ እንዳልሰማ ሆኖ ቆይቷል። እርግጥ ነው የተወሰኑ በሙስና ተዘፍቀው ተገኙ የተባሉ እንዲከሰሱ ተደርገው ነበር። ግን በትልልቅ የሙስና ወንጀሎች እስከአፍንጫቸው ተዘፍቀው ሀገርንና ሕዝብን እስከጥግ ሲዘርፉ የነበሩ ዋነኞቹ ሙሰኞችና ሌቦችን መክሰስና ማሰር አልተቻለም ነበር።

ምክንያቱም ዋነኞቹ ሙሰኞችና ሌቦች የገዥው መደብ አካል በመሆናቸው "ሰማይ አይታረስ ንጉሥ አይከሰስ" በሚለው ብሂል የሚመራው "ዘመነ አብዮታዊ ዴሞክራሲ(አውቶክራሲ)" ንጉሦችን መክሰስ አይፈልግም ነበረና። ንጉሦችን ቢነካ ኖሮ ደግሞ ፀረ ሙስና ራሱ ውሃ ውስጥ እንደገባ ሳሙና ሟምቶ ይቀር ነበረና ነው ነገሩ።

ሙስና ቃሉ የግዕዝ ነው፤ "አማሰነ" የሚለው የቃሉ መገኛ የግዕዝ ግስ "አባከነ" "አጠፋ" ከሚሉት የአማርኛ ቃላት ጋር ተመሳሳይ ነው። አማሰነ የሚለው የግዕዝ ግሳዊ ቃል ስም ሲሆን "ሙስና" የሚለውን ይወልዳል። ሙስና በአማርኛ ጉቦ ከሚለው ቃል ይቀራረባል።

**ማን እንደዘረፈኝ ... ልቤ እያስተዋለ**
**የለመደው አፌ "የመንግሥት ያለህ አለ!**

የሚለው ስነ ቃላዊ ግጥምም ዘራፊዎቹ መንግሥት ነኝ ባይ አሸባሪዎቹ እንደነበሩ ያሳየናል።

የቀድሞው ፌዴራል የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ይሠሩ የነበሩ ሠራተኞች በአንድ ወቅት እንደነገሩኝ፤ ለሚሠሩት የስኳር ፕሮጀክት መረጃ የሚሰጥ ቢጥሌ መጽሔት (ቡክሌት) እንዲያዘጋጁ በመመሪያ ትዕዛዝ ይወርድላቸዋል። ሠራተኞቹም ትዕዛዙን ተቀብለው መጽሔቱን ለማዘጋጀት ሥራቸውን ጀመሩ።

ታዲያ በዚህ መሐል የተወሰኑ የፋብሪካዎቹ ፕሮጀክት ግንባታዎች ለማየት ጓጉ፤ ግንባታው በሚካሄድባቸው ቦታዎች አንድ ሁለቱን ቢጎበኙ ለሥራው እንደሚረዳቸው ስላመኑ፤ ለሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ አቀረቡ። "መጀመሪያ በተሰጣችሁ ትዕዛዝ መሠረት ጽሑፉን ጨርሱና ትሄዳላችሁ" የሚል ምላሽ ተሰጣቸው። ጽሑፉን እንደጨረሱ ተጨማሪ የመስክ ሥራ ሲጠይቁ "የጻፋችሁት በቂ ስለሆነ መስኩ አያስፈልግም" ተባሉና ጽሑፋቸው እንጎቻ በሚባለው መጽሔታቸው ታትሞ ተሠራጨ።

መናገር የፈለኩት ስለመስክ መሄድና መቅረት፣ ስለመጽሔት መታተምና መሠራጨት አለመሆኑ ይሰመርበት፤ መዘዘኞቹ የስኳር ፋብሪካ ግንባታዎች ለሚዲያ ፍጆታና ዕይታ ብቻ ተብሎ መጽሔት ይታተምላቸው እንደነበር ለማሳየት ነው ጉዳዩን ያነሳሁት። እንጎቻ መጽሔቷን ታትማ ወጥታ በወቅቱ ሳነባት የሚያጓጉ ነገሮች ነበሩዋት። ኢትዮጵያ በስኳር ፋብሪካዎቹ ግንባታ ምርታማና ውጤታማ እንደምትሆን የሚያትቱ ጽሑፎችን ይዛ ነበር የወጣችው።

ከጽሑፎቹ መካከል ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ በቡና ላኪነት ትልቁን የውጪ ምንዛሪ የምታገኘው ሀገራችን በስኳር የውጪ ንግድ ገቢ፤ የቡናን ቀዳሚ የውጪ ገቢ ቦታ ትረከባለች የሚል ሀሳብም ነበረበት። እነኩባን በስኳር ኤክስፖርት ትፎካከራለች ትቀድማች፤ በፋብሪካዎቹም ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል ያስገኛሉ፤ ብዙ ከተሞች ይስፋፋሉ፤ ይመሠረታሉ የሚሉ ሕልሞችን (ዕቅዳችን ለማለት ስለከበደኝም እንደሆነ እወቁልኝ) ይዛ ነበር።

ሕልሞቹ ሕልም ሆነው እልም ብለው ቀሩ። የስኳር ፕሮጀክቱ እንደስኳር ሟሟ፤ የወቅቱ ባለሥልጣኖች በስኳር ሙስና ተዘፈቁ። በዚያን ጊዜ እየዳኸ የነበረው ሙስና፤ ቀና ብሎ በኩራት መራመድ፤ አልፎ ተርፎም በፈጣን ሪከርድ በአደባባይ መሮጥ ጀመረ።

አሥር ስኳር ፋብሪካዎች ይከፈታሉ ተብሎ፤ ለግንባታዎቹም ከውጪ ገንዘብ በብድር መጣ፤ በተመረጡት ቦታዎች ገበሬዎች እንዲለቁ እንዲፈናቀሉ ተደረገ፤ ሕዝቡ ቅር እያለው ማለት ነው። ሕልሙ ሕልም ሆኖ ገንዘቡም ባክኖ፣ የሙሰኞች ኪስ ማድለቢያ ሆኖ ቀረ።

ሌሎቹን ሙስና ጉዳዮች ብናነሳ ቦታ አይበቃንም። ሜቴክ ብቻ የዘረፈው በራሱ ምትክ የለሽ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ሲነገረን የነበረው ነገር ግን፤ "ባለሁለት አኃዝ ዕድገት አስመዘገብን ተብሎ ነበር"። የተመዘገበው ዕድገት ግን አልታይ ያለን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ተመዝግቦ ምቀኞች አጥፍተውት ይሆን እንዴ? አንዳንዳንዶች ለሙስና እንደ ኢሕአዴግ ሥርወ መንግሥት ምቹ ዘመን አልነበረም ይላሉ፤

ከደርግ ዘመን ጋር ሲያነፃፅሩት ማለት ነው። በደርግ ጊዜ የሠርቶ አደሩ የቁጥጥር ኮሚቴ የሚል ነገር ነበር። ዓላማው ጉቦን መከላከል ነበር፤ ሆኖም ጉቦን መከላከል ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ጉቦ የመቀበል ነገር ቢኖርም ሙስና ተስፋፍቶና ተንሠራፍቶ ሀገራዊ በሽታ መሆን የጀመረው ግን በኢሕአዴግ ዘመን መሆኑን ይናገራሉ።

በርግጥ ያለንበት ወቅት ስለሙስና ሳይሆን ስለሕልውና የምናስብበት ጊዜ ነው። እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚሉ አህዮች እኛ ሀገር ካልመራን አቧራ እናቦናለን፣ እናሸብራለን፣ እንበታትናለን ብለው ተነስተዋል። ለሀገር የማያስቡ የራሳቸውን ጥቅም የሚያሳድዱ መሆናቸውን ማሳያ ይሆናል። የተነገደበት ሀገር ወዳዱ የትግራይ ሕዝብ እያየው ነው። ከድህነት ማጥ እናወጣሀለን ብለው፤ ልጁን ለጦርነት እየማገዱት አባትና እናትን ኀዘን ጭንቀትና ድህነት አዘቅት ውስጥ እየከተቱት መሆኑ እርግጥ ነው።

ግን ያለፉት ሦስት የለውጥ ዓመታት በርካታ አመርቂ ሥራዎችን ተሠርተውበታል። በሙስና እየታመሰ የነበረው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ሥራ እንኳ የተነቃቃውና ውጤታማ የሆነው በለውጡ ነው። የመጀመሪያው እና የሁለተኛው ዙር ግድብ ሙሌት ቀደም ሲል የተካሄደ ሲሆን ሶስተኛ ዙር ደግሞ በቀጣይ እንደሚካሄድ ይጠበቃል ።

በቀጣይ አዲሱ ዓመት ደግሞ ከግድቡ የሚለቀቀውን የኤሌክትሪክ ብርሃን ዜጎች በጉጉትና በናፍቆት እየጠበቁት ነው። ክረምቱን ጠብቆ ሲከናወን የነበረው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ የሀገራችንን ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስጠራ ነው። ሌሎች ብዙ አመርቂ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ይህም ሆኖ ግን ሀገሪቱ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ብዙ ቅድሚያ የሚፈልጉ አንገብጋቢ ጉዳዮች በመኖራቸው አጠቃላይ የፀረ ሙስና ሥራው ተቀዛቅዞ ቆይቷል ማለት ይቻላል። ለውጡን ሊያናውጡ የሚፈልጉ አሸባሪዎች በየቦታው ሁከት ሲፈጥሩ ቆይተዋል። አሁን ያለው የአሸባሪዎቹ ግርግር ተጨምሮበት አሁንም ሁከቱ አላባራም።

አብዛኛው ሀገር ወዳድ ዜጋ የሀገርን ሕልውና ለማስከበር ሲታገል፤ በጎን ተሸሽገው ሙስናቸውን የሚያሳድዱ የውስጥ አርበኞችና ጥቅም አሳዳጅ ሌቦች ምቹ ሁኔታን አግኝተዋል። አጋጣሚው ሀገር የሚመዘብሩ ሙሰኞች እንዲበዙ አድርጓል። እነዚህም የሀገር ጠላቶችና ባንዳዎች ናቸው።

ከዚህ አኳያ የሃገር ሕልውናን የማረጋገጥ ሥራው እንዳለ ሆኖ ለሃገርና ለሕዝብ ዕድገት ጠንቅ ሆነውን ሙስናን መከላከል ሥራም ጎን ለጎን አብሮ ሊሠራ ይገባል። በመንግሥት መሥሪያ ቤት ብቻ እየዞሩ ገቢህ ስንት ነው? መመዝገብ ብቻ አይበቃም። ተቋማትን ነፃና ገለልተኛ አድርጎ ከማደራጀት፣ ብቁ አመራሮችንና ባለሙያዎችን ከመመደብ፣ ሕግና ሥርዓት በማስፈን ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ ትልልቅ ሥራዎችን ማቀድ መተግበር ያስፈልጋል። ዛሬ ዛሬ **በሜጋ ፕሮጀክቶች አካባቢ የታየውን የፀረ ሙስና ትግል ማስቀጠልም ወሳኝ ነው ፡፡**

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ክረምት እና የጫማ ፋሽን



ተገኝ ብሩ

በበጋው ወራት ሙቀት የሚቋቋም ቀለል ያለና ምቾት እንዳይነሳን መርጠን ያደረግናቸውን ጫማዎች ወልውለን ወደ መደርደሪያ የምንመልስበት ወቅት ላይ ነን። በምትኩ የክረምትን ቅዝቃዜ የሚቋቋሙ፣ እርጥበት ምቾት እንዳይነሳን የሚያደርጉ ጫማዎችን ከያሉበት አውጥተን የምንጫማበት፣ ከሌለንም ወደ ጫማ መሸጫ ሱቆች ጎራ የምንልበት ወቅት አሁን ነው። በበጋ ወራት በርካታ የጫማ የፋሽን አማራጮች እንዳሉ ሁሉ በክረምቱም ወራት ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ የፋሽን አማራጮች አይጠፉም። ፋሽን ተከታዮች ወቅቱን መሠረት ያደረጉ ጫማዎችን ለመሸመት ወደ ገበያ የሚያቀኑት ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ከግምት አስገብተው ነው።

የመጀመሪያውና ዋነኛው ጉዳይ የሚጫሙት ጫማ የወቅቱን አየር ንብረት ተቋቁሞ የክረምቱ ቅዝቃዜ ምቾት ሳይነሳ ወደ በጋ ወራት ያሻግራል የሚለው ከጥንካሬ ጋር የተያያዘ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የጫማው ተጠቃሚ የሚሰጠውን ምቾት ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ እንደዘመነኛ ሰው ጫማው ከራስ ምቾት ባለፈ ለሚመለከተው ሰው የሚፈጥረው ውበትና የወቅቱ ፋሽን መሆኑ ከግምት ሊገባ ይችላል።

በክረምት ወራት ጥንካሬ፣ ምቾት፣ ውበትና ወቅቱን የዋጁ ጫማዎች በብዙዎች ይመረጣሉ። በክረምት ወራት ሸማቹ ብቻ አይደለም ከወቅቱ ጋር ለመራመድ ጥረት የሚያደርገው። የጫማ መሸጫ መደብሮችም ወቅቱን ታሳቢ ያደረጉ ለክረምት የሚሆኑ ጫማዎችን ከመደርደሪያቸው ፊት ላይ ማሰለፋቸው የተለመደ ነው። በዚህም ምክንያት የጫማ ብቻ ሳይሆን የአልባሳትም ዋጋ በተፈላጊነታቸው የተነሳ ከበጋ ወቅት ይልቅ ከፍ ሲል ይስተዋላል።

በዚህ ወቅት በተለይም በወጣቶች ተመራጭ የሆኑ ዘመናዊ ጫማዎች በሱቆቹ ውስጥ ተበራክተው ይታያሉ። እንደ አልባሳት ጫማም ወቅቱን ጠብቆ የሚለበስ እንደመሆኑ በበጋና ክረምት ታሳቢ ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው። ወቅቱን መሠረት አድርገው ለተለያዩ ዝግጅቶች ከአልባሳት ጋር አብረው እንዲሄዱም የሚሰናዱ ናቸው። በዚህም ምክንያት ሰዎች መርጠው የሚጫሟቸው የጊዜው ፋሽን ልኬትን ያሟሉና ገበያው ላይ ተፈላጊ የሆኑ ጫማዎችን ለደንበኞቻቸው አዘጋጅተው የሚያቀርቡ ሱቆች በዚህ ወቅት ደንበኞቻቸውን በማስተናገድ ተጠምደው ይገኛሉ።

የክረምቱን ወቅት አስመልክተን በመዲናችን አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ የተዘጋጁ አልባሳትና ጫማ መሸጫ መደብሮች ውስጥ ስንዘዋወር አይናችን አዳዲስ በገቡ የዘመኑ ዲዛይነሮች የተጠበቡባቸው የክረምት ወቅት ጫማዎች ላይ አረፈ። አይናለም ጥላሁን የሽያጭ ሠራተኛ ነች። ከ1 ዓመት በላይ በዚህ ሙያ ውስጥ ቆይታለች። ፒያሳ ከአምፒር ሲኒማ ጀርባ ካሉ የአልባሳትና ጫማ መሸጫ ሱቅ ውስጥ በሥራ ላይ ነች።

በምትሠራበት ሱቅ ውስጥ በአብዛኛው ከቱርክና ከዱባይ የመጡ ዘመናዊ የክረምት ጫማዎች በብዛት ይገኛሉ። በደንበኞቿ በአብዛኛው የሚፈለገው የውጪ ጫማዎች መሆኑን የምትናገረው አይናለም፣ ከክረምት ወቅት ጋር ተስማሚ የሆኑ የሀገር ውስጥ የጫማ ምርቶች ብዙም ባለመኖራቸው ሸማቹ ወደ ውጪ ምርቶች እንደሚሳብ ታስረዳለች።

የጫማ ገበያው እንደ ልብስ ገበያው ፈጣን የሆነ የመቀያየር ባህሪ ባይኖረውም ጫማዎችም በየወቅቱ በአዲስ መልክ ወደ ገበያው በዲዛይነሮች ተሠርተው እንደሚቀርቡ የምትናገረው አይናለም፣ ተጠቃሚዎችም አዳዲስና በሌሎች ያልተለበሱ ጫማዎች ገዝተው ማድረግን እንደሚመርጡ ትናገራለች። አብዛኞች ደንበኞቿ በወጣትነት እድሜ ላይ የሚገኙ ቢሆኑም የጫማ ፋሽን ተከትለው የሚገዙ አልፎ አልፎ ከፍ ባለ እድሜ ላይ የሚገኙ ሰዎች መኖራቸውንም ታስረዳለች።

ከወጣቶች በስተቀር በአብዛኛው ወደ ሱቅ የሚመጡ ደንበኞቿ ፋሽንን ሳይሆን አብዛኛው ጊዜ ትኩረት የሚያደርጉት ክረምት ከሆነ ለክረምት የሚሆናቸውን ለመግዛት ነው።በጋ ላይ ደግሞ ሙቀት የሚከላከል ጫማ ብለው እንደሚጠይቁ ትናገራለች። በሱቋ ውስጥ ከብር 600 እስከ 3500 ብር ድረስ ዋጋ ወቶላቸው ለሽያጭ የተዘጋጁ የክረምትም የበጋም ወራት ጫማዎች በየረድፉ ተደርድረው እንደሚገኙም አስተውለናል።

ጫማዎቹ የተሠሩበት ወይም የተዘጋጁበት ጥሬ እቃ፣የዲዛይንና ውበት አይነት የተለያየ ነው። እንደየጥራት ሁኔታቸውም የዋጋቸው መጨመርና መቀነስ ሁኔታ የተለያየ ነው። በተለያየ ስሪት (ብራንድ) ተፈብርከው የቀረቡ የቆዳና የእስኒከር ጫማዎች በየምድባቸው ዋጋቸው የተለያየ ነው። የተለመዱ የጫማ ብራንዶች አዲዳስ፣ ፑማ፣ ስኬቸርስ፣ ጆርዳንና ናይኪ የተሰኙ ጫማዎች በቁጥር ከፍ ብለው የሚታዩና በሸማቹ ዘንድም የሚፈለጉ ናቸው።

አካባቢው ላይ ባሉ የጫማ መሸጫ ቤቶች የሀገር ውስጥ ስሪት የሆኑ ጫማዎችን እንደ ልብ ማግኘት ከባድ መሆኑን ተረድተናል። በእርግጥ እዚያ አካባቢ ባሉ ሱቆች የሀገር ውስት ስሪት ጫማዎች አይገኙ እንጂ በሌሎች አካባቢ ባደረግነው ቅኝት በተለይም ከቆዳ የተሠሩ የክረምት ወቅት ጫማዎች በብዛት ገበያው ላይ መመልከት ችለናል።

ነገር ግን በዚሁ አካባቢ የሚገኙ ባለሱቆችን ስለምን ለደንበኞች የሀገር ውስጥ ጫማዎች ማቅረብ እንዳልቻሉ ጠየቅን። የሀገር ውስጥ ጫማዎች በብዛት የማያቀርቡበትን ዋንኛ ምክንያት አይናለም ስታስረዳ፣ ደንበኞቿ በአብዛኛው የሚመርጡት የውጪ ጫማዎችን በመሆኑ እሷም የደንበኞቿን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለገበያ እንደምታቀርብ ታስረዳለች።

የሀገር ውስጥ ጫማዎች በአብዛኛው በዲዛይን ምክንያት ደንበኞቿ እንደማይመረጡ የምትናገረው አይናለም፣ የዚህ ዋነኛ ምክንያትም ከዲዛይን ውበት ጋር በተያያዘ የሀገር ውስጥ ምርቶች ሳቢ አለመሆናቸው ወይም የውጪዎቹ ምርቶች የተሻለ ውበት ተላብሰው ስለሚገኙ መሆኑን ታስረዳለች።

መዓዛ ሙሉነህ ሱቋ ውስጥ በጫማና ልብስ ሽያጭ ተሰማርታ ትገኛለች። እሷም ሱቅ ውስጥ ሀገራዊ የሆኑ ጫማዎች የሌሉ መሆኑን አጫውታናለች። የሀገር ውስጥ ጫማዎች በብዙዎች እንደማይመረጡና የወቅቱን ፋሽን በተከተለ መልኩ በምርጫ ለገበያ አለመቅረባቸው ምክንያት መሆኑን ትናገራለች።

አገራዊ ኢኮኖሚን በማጠናከር ከውጪ የሚመጡ ምርቶችን መቀነስና የሀገር ውስጥ ምርት ገበያው ላይ በስፋት እንዲገኝ ማድረግና ማበረታታት ተገቢ መሆኑ አያከራክርም። የሀገር ውስጥ ጫማዎች በስፋት ገበያው ላይ አለመገኘት በጅምር ደረጃ ያሉት የዘርፉ አምራቾች የተሻለ ገቢ እንዳያገኙ እንቅፋት እንደሚሆን ይታመናል።

ገበያው ላይ ያሉ ምርቶች አብዛኞቹ ከውጪ የሚገቡ በመሆናቸው ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሀገር ውስጥ ጫማ አምራች ኢንዱስትሪዎች ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው አስተያየት ሰጪዎች ይናገራሉ። የሀገር ውስጥ ጫማ አምራቾች በተለይም የቆዳ ውጤት አምራች ኢንዱስትሪዎች ገበያው ላይ የተሻለ ምርት አምርተውና አቅርበው ከሌላው ጋር ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ በተለይም ከዲዛይንና ውበት ጋር በተያያዘ ሊያስቡበት እንደሚገባም የብዙዎች እምነት ነው። በገበያው ንቁ ተሳታፊ ያላደረጋቸው የሚያመርቱበት ማሽንና ቴክኖሎጂም ከዘመኑ ጋር አብሮ መጓዝ እንዳለበት ይታመናል።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ወይ በጋራ እንዘን ወይም ዝም እንበል

አቤል ገ/ኪዳን

የነፍሰ በላው ናዚ ጭፍጭፋ ካለፈ በኋላ በ1946 ማርቲን ኒሞለር የተሰኘ የሉተራን ቄስ የተናዘዘው ታዋቂ አባባል አለ:: ይህ አባባል ‹‹መጀመሪያ ወደ ሶሻሊስቶች መጡ፣ ሶሻሊስት ስላልሆንኩኝ ምንም አልተናገርኩም ነበር:: ቀጥሎ ወደ ንግድ ማኅበር መጡ፣ የነጋዴዎች ማኅበር ውስጥ ስላልሆንኩኝ  ምንም አልናገርም ነበር:: ቀጥሎ ወደ አይሁዶች መጡ፣ አይሁድ ስላልሆንኩኝ ምንም አልተናገርኩም ነበር:: በመጨረሻም ወደ እኔ መጡ:: የሚጮህልኝ አንድም ሰው አልተረፈም ነበር›› ይላል። ማርቲን ኒሞለር ይህንን ያለው በናዚ ጭፍጭፋ ወቅት ምሁራን እና የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የናዚን ጭፍጨፋ ላለማውገዝ ዝምታ በመምረጣቸው ምክንያት ነበር::

ዛሬ ላይ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን በዚህ አይነት ድንዛዜ ውስጥ ያለን ይመስላል። ሁላችንም ቄስ ማርቲንን ሆነናል።ጥቃት እኛ ጋር የሚደርስ አልመስለን ብሏል።እንዲያውም ሲመችን ለአጥቂ በግልጽም ስልታዊም ድጋፍ የምንሰጥ ነን።

ነፍሳቸውን ይማረውና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ስለዚህ የኢትዮጵያውያን ባህሪ በአንድ መጽሐፋቸው ላይ ሲገልጹ ‹‹ኢትዮጵያውያን አምባገነንን እንጂ አምባገነንነትን አይቃወሙም›› ይላሉ። እንደሳቸው አባባል ሕዝባችን የሚቃወመው አምባገነንነትን ሳይሆን የሚቃወመው አምባገነኑ የሱ ወገን ካልሆነ ነው።ይህም ማለት አምባገነኑ ምንም ያህል አምባገነን ቢሆን የሱ ብሔር የሱ ሃይማኖት የሱ ሰፈር ከሆነ አይቃወምም። ድጋፍ እና ከለላ ይሰጠዋል። አምባገኑን ያጸድቅለታል። ይሁን ብሎ ይቀበለዋል። በተቃራኒው አምባገነኑ ከሱ ወገን ካልሆነ ይነቅፈዋል፣ ከዓለም አምባገነኖች ሁሉ ከፉው እሱ እንደሆነ ተናግሮ አይጠግብም። መወገድ እንዳለበት ሲሰብክም ፋታ አይኖረውም። በዚህም የተነሳ የጋራ የምንለው ጀግና እንደሌለን ሁሉ የጋራ የሆነ አምባገነንም የለንም። በዚህም የተነሳ ተራ በተራ እንሞታለን። ብዙዎች ዛሬ እነ እገሌን ያሸበረው ኃይል ነገ እነሱን የሚያሸብር አይመስላቸው ። ዛሬ እገሌን የገደለው ኃይል ነገ እነሱን ሊገድል እንደሚችል ይረሳሉ። ሀቁ ግን መግደል ሱስ ይሆናል ነው። ዛሬ በእነ እገሌ ላይ የተጀመረ ግድያ ነገ እነሱ ጋር እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለውም። ወይም ምንም ማስተማመኛ የለውም።

ዝነኛው የብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል በአንድ ወቅት የተናገረው ዝነኛ ንግግር አለ። ቸርችል እንዲህ አለ ‹‹አሽቃባጭ ማለት አዞው እኔን ቢበላኝ እንኳ የሚበላኝ ከሁሉም መጨረሻ ነው ብሎ አዞውን የሚመግብ ነው››። ቸርችል ይህን ያለበት ምክንያት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት አንዳንድ የአውሮፓ ሀገራት ናዚን ባለመቃወም ዝምታን በመምረጣቸው ነው።ሀገራቱ ዝምታን የመረጡት ዝም ካልን እኛን አይነካንም ብለው በማሰብ ነበር።ነገር ግን ዝምታቸው አልጠቀማቸውም። ‹‹ዝምታ ለበግም አልበጀት›› እንዲሉ ሂትለር እንኳን ዝም ያሉትን በይፋ ወዳጆቹ የሆኑትንም አልማረም። ዛሬም በኛ ሀገር የሆነው ይህ ነው። የአንዱ ብሔር ለቅሶ ሌላውን አልቀሰቀሰውም። ሁሉም ድምጹን አጥፍቶ ተራውን ይጠብቃል።

እስኪ ሩቅ ሳንጓዝ የሰሞኑን ክስተቶች እንመልከት። መጀመሪያ ጎንደር ላይ ያ አሳፋሪ ክስተት ተከሰተ። ከዚያ አሁን በቅርቡ የጋምቤላው ቀጠለ። አሁን የወለጋው ሰለሰ። በነዚህ ሶስት ክስተቶች ላይ የተፈጸመው ድርጊት በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። ያዘነው ሰው ግን የተለያየ ነው። ለምን? አንዱ ቦታ ሲጠቃ ዝምታን መርጦ የነበረው ወገን ሌላው ጋር የደረሰብኝ ጥቃት ይደርስብኛል ብሎ ስላላሰበ ነው። የጎንደሩን ጥቃት በጋራ ተቃውመነው ቢሆን ኖሮ የወለጋው አይከሰትም ነበር።አሁን የወለጋውን አንድ ወገን ሲቃወም ሌላው ዝም ብሏል። ጠላታችን በተራ በተራ ያስለቅሰናል። የሁላችንም ብስጭት ግን ለምን አለቀስን ሳይሆን እኔ ሳለቅስ እነ እገሌ ለምን አላገዙኝም የሚል ነው። እነ እገሌ ደግሞ ዛሬ እኛ ስናለቅስ ዝም ያሉት አያገባንም ከእኛ ጋር አይገናኝም፣ እኛም ጋር አይደርስም ብለው በማሰብ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ይቆይ ይሆናል እንጂ በዚህ አሰላለፋችን በተራ ከማለቅ የተለየ እጣ ፈንታ አይኖረንም።

የምንኖርበት ዓለም ግሎባላይዜሽን የሰፈነበት ዓለም ነው። የጋራ ጥቅም ብዙ ስለሆነ የጋራ ደህንነት ላይ ብዙ ይሠራል። እንኳን ሀገራት ዓለም ራሱ የምትመራው ብዙኃኑ በተስማሙበት የጋራ ሕግ ነው። ማንም ሀገር በነጠላ ራሴን ችዬ እቆማለሁ አይልም። ኃያላኑ ሁሉ አንዳቸው በሌላቸው ላይ ጥገኛ ናቸው።ለዚህም ነው አንዱ ሀገር ላይ የተፈጠረ ችግርን እንደጋራ ችግር የሚያዩት። ለዚህ ነው ኔቶ የተፈጠረው። ለዚህ ነው አሜሪካ ላይ አንድ የሽብር ጥቃት ሲፈጸም መላው የምዕራቡ ዓለም አብሮ ከማዘን እስከ አብሮ መዝመት የሚደርሰው። እኛ ጋር ነገሩ በተገላቢጦሽ ነው። አንዱ ጋር የሚፈጠር ክስተት የሌላው የፖለቲካ ነጥብ ማስቆጠሪያ ግብዓት ነው። ከባህር ወዲህ እና ከባህር ወዲያ ያሉት አሜሪካ እና አውሮፓ በጋራ ህልውናቸው ላይ ተባብረው ሲሠሩ እኛ ጋር አብሮ የተዋለደው ሕዝብ አንዱ ሲሞት ሌላው ዳር ይዞ በዝምታ ያያል። ይሄ ፈጽሞ አያዋጣም። ከተቃወምን በጋራ እንቃወም። አልያም ግን ዝም እንበል።በፈረቃ ማዘን እስካሁን መፍጠር የቻለው የማኅበራዊ ሚዲያ የብሽሽቅ መንፈስን እንጂ ሌላ ምንም ነገር አይደለም። ይህ ደግሞ ለዚህች ምስኪን ሀገር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንጂ የሚፈይዳት አንዳች ነገር የለውም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# አሸባሪው ሸኔ፡- የሕወሓት ጽንስ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

አሸባሪው ሸኔ የአሸባሪው ሕወሓት ጽንስ ነው። ለፖለቲካው እንዲመቸው፣ ለስልጣኑ እንዲቀናው በተንኮሉ ልክ አምጦ የወለደው የእኩይ ሀሳቡ በኩር ነው። በለውጡ ማግስት የታየው ሀገራዊ መነቃቃት የክፋት ሕልውናቸውን ፈትኖት መቋቋም ስላልቻሉ ሕወሓት ወደለመደው ጫካ፣ሸኔም በሕወሓት ጭንብል ሀገርና ሕዝብ ማስጨነቁን ቀጥሎበታል። ትርፋቸው በንጹሓን ደም እና ሰቆቃ መቆመር ነው፤ ይኸው ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የአሸባሪው ሕወሓትን የግፍ አገዛዝ አሸንፋ ቀና ባለችበት የለውጡ ማግስት እነኚህ የእፉኝት ልጆች መርዛቸውን እዚህም እዚያም እየረጩ ሀገር በማወክ ላይ ናቸው። መርጠው እየገደሉ፣ መርጠው እያሰቃዩ በወንድማማቾች መካከል መቃቃርን ለመፍጠር ጎንበስ ቀና በማለት ላይ ናቸው። የነዚህን ኃይሎች ዓላማ ስልጣንና ስልጣን ብቻ ነው።

እስኪ እንጠያየቅ ... ሕወሓት ለኢትዮጵያ ምን ነበር? ያለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ለእኔና ለእናንተ ምን ማለት ነበር? ልክ እንደ ሕወሓት አስተሳሰብ ሁሉ የሸኔ አስተሳሰብም ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ነው። ሀገር ለምንናፍቅ ለእኔና ለእናንተ፣ ኢትዮጵያዊነት ለሚርበን ለእኔና ለእናንተ እንጂ፣ ማሰብና ማገናዘብ ለማይችሉት ለሕወሓትና ለሸኔ የኢትዮጵያ መፍረስ ምናቸውም አይደለም። በወደመችና ታሪክ በሌላት ሀገር ላይ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያውቃሉ። ታሪክ አበላሽተው፤ ትውልድ አውድመው በክፋት ልብ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ጥርሳቸውን የነቀሉበት ተግባራቸው ነው።

ለእኔና ለእናንተ እንጂ ለነሱ የኢትዮጵያ መኖርም ሆነ አለመኖር ትርጉም የለውም። ለዚያ እኮ ነው በመግደል ማሸነፍን የሚለማመዱት። ለዚያም ነው ንጹሓንን አሰቃይተው ጀግንነታቸውን ለማሳየት የሚሞክሩት። ተከባብሮ የሚኖርን ሕዝብ በተንኮል ሀሳባቸው ለማባላት የሚፍጨረጨሩት ለዚሁ ነው። ጭር ሲል አይወዱም። የኢትዮጵያን ሰላምና ልማት የማይፈልጉ ኃይሎች ናቸው። እነዚህ ኃይሎች አሁንም በሕዝብና በመንግሥት እንዲሁም በሕዝቦች መካከል መለያየትን ፈጥረው የራሳቸውን ስውር ዓላማ ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ናቸው።

እነዚህን ኃይሎች ለማሳፈር አንዱ ሕዝብ ስለሌላው መጮህና ‹ያገባኛል› ሊል ይገባል። በየትም ቦታ የሚፈስ የአንዱ ደም የሌላው ወንድሙ ደም ነው። በዚህ የሀሳብ ኅብራዊነት ውስጥ በቅለን ስንጸድቅ ብቻ ነው የጽንፈኞቹን ህልም የምናወድመው። በዚህ የሀሳብ ልዕልና ውስጥ ስንቆም ብቻ ነው ሕወሓትንም ሆነ ልጁን ሸኔን ታግለን የምናሸንፈው።

ለሀገር የሚያስብ ሀገርን አይጎዳም፤ትውልድን አያመክንም። ለወገን የሚቆረቆር በወንድማማቾች መካከል ጸብን አይዘራም፤ ንጹሓንን አይገድልም። አሸባሪዎቹ ሕወሓት እና ሸኔ ለሀገርና ለሕዝብ ታግለው አያወቁም። በየትኛውም መመዘኛ ቢታይ ሀገር እያጠፉ ለሀገር መታገል፤ ሕዝብ እየጨፈጨፉ ለሕዝብ መታገል የሚባል ነገር የለም። እነዚህ ኃይሎች ዓላማቸው ሀገር ማውደም እንዲሁም ተከባብሮና ተፋቅሮ የሚኖረውን ሕዝብ መለያየት ነው። መሠረት በሌለው የፖለቲካ እሳቤያቸው ሕዝብን ከሕዝብ፣ ብሔርን ከብሔር አጋጭተው እፎይ ማለትን የሚከጅሉ ናቸው።

ሕዝብ የእነዚህን እኩይ ኃይሎች ዓላማ ተገንዝቦ አንድነቱን መጠበቅ እንጂ ኮሽ ባለ ቁጥር የወንድማማች ጽናቱን መነቅነቅ የለበትም። ሕወሓትና ሸኔ የዚህ ዘመን ቃየሎች ናቸው። የወንድሞቻቸውን ደም የሚጠጡ፣ በወገኖቻቸው ሞት ጮቤ የሚረግጡ ሴንግኖሳዊያን። ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም። ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቢረዱ ኖሮ በዚህ ልክ ወልዳ ባሳደገቻቸው ሀገራቸውና በወገናቸው ላይ ባልጨከኑ ነበር። በመግደል የሚረኩ፣ ዓላማቸውን በመግደል የሚያስፈጽሙ የሰይጣን ጭፍሮች ናቸው።

ሰው በመግደል የፖለቲካ ትርፍ አይገኝም። የአንድ ብሔርን ዘር ለይቶ በማጥቃት በወንድማማቾች መካከል ጠብን ከመፍጠር ባለፈ የፖለቲካ ጥያቄን አይመልስም። አሁን ላይ እነዚህ ሁለት ኃይሎች የያዙት ዓላማ አንዱን ብሔር በማጥቃት ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ፣ አንድ ብሔርን ለይቶ በማግለል ሕዝብን በመንግሥት ላይ ማስነሳት ነው። የሕወሓት ማንነት ለብዙዎቻችን ግልጽ ነው። ያለፉትን ሃያ ሰባት ዓመታት እንተውና ባለፉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ በምን አይነት ሀገራዊና ማኅበራዊ ስቃይ ውስጥ እንደነበርን ሁላችንም የምናውቀው ነው።

እነዚህን ኃይሎች ለመታገል የአንድነት ፍቅራችን ግድ ይለናል። እኩይ ዓላማቸውን ተገንዝበን የክፋት ሴራቸውን በወንድማማችነት ስሜት ማውደም እንጂ ኮሽ ባለ ቁጥር ለመለያየት መፍጠን የለብንም። ሕወሓት በባከነ አስተሳሰብ የባከነችን ሀገር ፈጥሯል። የዚህ ብኩን አስተሳሰብ ውጤት ከሆኑት ውስጥ ደግሞ አንዱ ሸኔ ነው። ገዳይነትን ከአባቱ ከሕወሓት ተቀብሎ ይኸው ሕዝብ እያስጨነቀ ነው። የእባብ ልጅ እባብ እንጂ የእባብ ልጅ እርግብ ሆኖ አያውቅም። የእባብ ልጅ ከመንደፍና መርዙን ከመርጨት በቀር ተፈጥሮ የለውም። ሕወሓትና ሸኔም እንደዚህ ናቸው። በአንድ ደረት ላይ የበቀሉ መንታ ጡቶች፣ ወተት ሳይሆን መርዝ የሚያመነጩ፣ ሕይወት ሳይሆን ሞት የሚነግዱ።

አሁን ላይ የሕወሓት ቡድን ያበላሻትን ኢትዮጵያ በአንድነት ስሜት መገንባት እንጂ አምጦ በወለደውና፣ የመርዝ እርጎ እያጠጣ ባሳደገው የሸኔ ቡድን ፍቅራችንን ማጣት የለብንም። ተባብረን በአንድነት የነዚህን ግብዓተ መሬት ማፋጠን እንጂ ለክፋታቸው እጅ መስጠት የለብንም። መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩ የሕዝቦችን ደህንነት መጠበቅና ወንጀለኞች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ነው። በዚህ ረገድ መንግሥት የቤት ሥራውን አጠናክሮ እንደሚወጣ በማመን እስከዚያው ግን እነዚህን እኩይ ቡድኖች በሚያሳፍር መልኩ በአንድነት መቆም ይኖርብናል።

በሕዝቦች መካከል እንዲሁም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለው አንድነት በእነዚህ ቡድኖች የክፋት ሀሳብ መላላት የለበትም። ዓላማቸው ምን እንደሆነ ተገንዝበን በፍቅራችን ልንጥላቸው መተቃቀፍ ይኖርብናል። የፍቅር ክራችን፣ የአንድነት ድራችን በእኩይ ኃይሎች እንዲላላ መፍቀድ የለብንም። ወንድማማችነታችን በክፋት ልቦች መጠልሸት የለበትም። የእኛ መለያየት ለጠላቶቻችን በር ይከፍታል። የእኛ መገፋፋት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ለተነሱት ሕወሓትና ሸኔ ኃይል ይሆናል። የምናሸንፋቸው በአንድነታችን ስንበረታ ነው። የምናንበረክካቸው አንዱ ለሌላው አለኝታ ሲሆን ነው።

የእፉኝት ልጆች ሥራቸው መግደል ብቻ ነው። ካልገደሉ ያልበረቱ የማይመስላቸው፣ ሕዝብ ካላስጨነቁ ያላሸነፉ የሚመስላቸው ናቸው። ዓላማውን ሀገር ያደረገ ግለሰብ ሰው አይገድልም። ዓላማውን ሕዝብ ያደረገ ቡድን ንጹሓንን ያለርህራሄ አይጨፈጭፍም። በነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች ውስጥ ግን ሀገር የለችም፤ሕዝብና ትውልድ ቦታ የለውም። ብቸኛ ዓላማቸው ኢትዮጵያን ማፍረስና ወደ ሕወሓት አስተሳሰብ መመለስ ነው። በብሔር ከፋፍለው ኢትዮጵያ አሳዛኝ የእርስ በእርስ እልቂትን ያስተናገዱ ሀገራት እጣ ፋንታ እንዲገጥማት ማድረግ ነው።

ከዚህ እውነት በመነሳት የእነዚህ ኃይሎች ዓላማ ምን እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ከትላንት እስከዛሬ አንዱ ብሔር ለሌላው ብሔር ጠላት ሆኖ አያውቅም። በሕወሓት የሀሰት ፕሮፖጋንዳ ግን ባለታሪክ ወንድማማቾች እንደጠላት ሲተያዩ ነበር። የእነዚህ ወንድማማቾች የክፋት ጠንሳሽ ሕወሓት ነበር። ምክንያቱም ሕዝቦችን ካላጋጨና ካላባላ ስልጣን ላይ የመቆየት እድል አይኖረውምና ነው።

ዛሬም እንደ ሰማይ ለራቀው ስልጣኑ በፍቅር የተሳሰሩትን ኢትዮጵያውያንን ለመለያየት በሸኔ በኩል አዲስ ክፋት እየጎነጎነ ነው። ይሄን ቡድን በተመለከተ ራሳችንን የምንጠይቀው ጥያቄ ይኖራል ... ሕወሓት የኢትዮጵያ የምንግዜም ጠላት ከሆነ፣ ሸኔ በሕወሓት ሰልጥኖ፣ በሕወሓት በልጽጎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እፉኝት ከሆነ ከእኛ ምን ይጠበቃል? ከእኛ የሚጠበቀው በአንድነት የክፋት ጉንጉናቸውን መበጣጠስ ነው።

አንዱ በሌላው ላይ ጣቱን ሳይቀስር በሰከነና በተረጋጋ መንፈስ ጠላቶቻችን ላይ የበላይ መሆን አለብን። ሕወሓትና ሸኔ ኢትዮጵያን ለማፍረስ አንድ ሆነዋል፤ እኛ ኢትዮጵያን ለማቆም አንድ ብንሆን ምን ይገርማል?! ሕወሓትና ሸኔ የብሔር ጦርነትና የዘር ፍጅት ለመፍጠር ቀን ከሌት እየሠሩ ነው። እኛ ኢትዮጵያን ለማስቀጠል በአንድነት ብንሰለፍ ችግሩ ምንድነው? ሕወሓትና ሸኔ በአንድ አይነት አስተሳሰብ አንድ አይነት ሆነው የቆሙ ናቸው፣ እኛ ለኢትዮጵያ ህልውና በአንድ አይነት አስተሳሰብ፣ አንድ አይነት ሆነን ብንቆም ምን እንጎዳለን? መልሱ ምንም ነው።

ጠላቶቻችን ባጠመዱልን የሞትና የመለያየት ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባ ምክራቸውን የሚያፈርስ የፍቅር ኃይል ያስፈልገናል። ጠላቶቻችን በቆፈሩልን የብሔር ጉድጓድ ውስጥ እንዳንወድቅ ሀሳባቸውን የሚሽር የአንድነት ጉልበት ግድ ይለናል። ጠላቶቻችን በደገሱልን የሞት ድግስ እንዳንታደም ህልማቸውን የሚያመክን የወንድማማችነት ስሜት ያስፈልገናል። ሕወሓትና የእንግዴ ልጁ ሸኔ በሀሳብም በተግባርም የሚሞቱት እኛ ስንበረታ ነው። ምክራቸውን ለማጥፋት፣ ሀሳባቸውን ለማምከን እኛ በአንድነት መቆም አለብን።

ዛሬ ላይ ኢትዮጵያን ለመጣል ተግተው እየሠሩ ነው። አንዱን ወገን በመግደል ለብሔር ጥላቻ ያለው ትውልድ ለመፍጠር እየታተሩ ነው። ንጹሓንን በመግደል፣ ሕጻናትን በመድፈር፣ ሴቶችን በማሰቃየት መልስ ለሌለው ጥያቄ መልስ እየፈለጉ ነው። ከሰሞኑ በምዕራብ ወለጋ የተከሰተው አማራ ተኮር የንጹሓን እልቂትም የዚህ አንዱ ማሳያ ነው። ከዚህ በፊትም በነዚህ ኃይሎች የተከሰተው የጅምላ እልቂትም ቡድኑ አንዱን ብሔር ከአንዱ ብሔር ለማጋጨትና ኢትዮጵያን ለማፍረስ እየሄደበት ያለው መንገድ የት ድረስ እንደሆነ አመላካች ነው።

በነዚህ ሁሉ ማስረጃዎች የቡድኑን ተልዕኮና ዓላማ መረዳት ይቻላል። እነሱ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ይኖራሉ፤ እኛ ደግሞ ኢትዮጵያን ለመጠበቅ እንኖራለን። ኢትዮጵያን የምንወድ እኛ ከነሱ ብዙ ነን። መካከላችን ፍቅር ሲኖር ደግሞ ጠላቶቻችንን ከእግራችን በታች ለማንበርከክ ኃይል እናገኛለን። እናም በፍቅር ጠላቶቻችንን እናንበርክክ። አሁን የሚያስፈልገን የጠላቶቻችንን ዓላማ ማወቅ ብቻ ነው። የጠላቶቻችንን ዓላማ ካወቅን ምን ሊያደርጉን እንደሚገድሉን፣ ምን አስበው እንደሚያሳድዱን መረዳት አይከብደንም።

የጠላቶቻችንን ዓላማ ካወቅን በነሱ ላይ የበላይ መሆን አይቸግረንም። እነርሱ በሁሉ ነገሯ የተሻለችውን ታላቋን ኢትዮጵያ ማየት አይፈልጉም። እነርሱ ከሕወሓት አስተሳሰብ የጸዳችውንና እውነተኛይቱንና ፍትሐዊቷን ኢትዮጵያን ማየት አይሹም። እነርሱ ኢትዮጵያ በልጽጋ፣ ሕዝቦቿም የተሻለ ሕይወት ሲመሩ ማየት ያማቸዋል። በዚህ ሁሉ ማስረጃ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት አሁናዊውንም ሆነ ቀጣዩን የሕወሓትንም ሆነ የሸኔን ዓላማ መረዳት እንችላለን።

ኢትዮጵያን መጠበቅ የሁላችንም ግዴታ ነው። ሕወሓት አምጦ በወለደው ሸኔ ምክንያት የድሮ ፍቅራችንን እንዳናጣ የዚህን ክፉ ቡድን ዓላማና ተልዕኮ መረዳት ይኖርብናል። ዓላማውም ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። የትናንቶቹ የጋምቤላና የወለጋ ጥቃቶች የታሪካዊ ጠላቶቻችን የሰኔዎች ሥራ አካል መሆኑንም መረዳት ተገቢ ነው።

**እስኪ እንጠያየቅ ... ሕወሓት ለኢትዮጵያ ምን ነበር? ያለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ለእኔና ለእናንተ ምን ማለት ነበር? ልክ እንደ ሕወሓት አስተሳሰብ ሁሉ የሸኔ አስተሳሰብም ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ነው:: ሀገር ለምንናፍቅ ለእኔና ለእናንተ፣ ኢትዮጵያዊነት ለሚርበን ለእኔና ለእናንተ እንጂ፣ ማሰብና ማገናዘብ ለማይችሉት ለሕወሓትና ለሸኔ የኢትዮጵያ መፍረስ ምናቸውም አይደለም:: በወደመችና ታሪክ በሌላት ሀገር ላይ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ያውቃሉ:: ታሪክ አበላሽተው፤ ትውልድ አውድመው በክፋት ልብ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ጥርሳቸውን የነቀሉበት ተግባራቸው ነው**

# ኢትዮጵያን የዓለም ተምሳሌት ያደረጋት አረንጓዴ አሻራ

**አንተነህ ቸሬ**

በ2011 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መሪነት በተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር (Green Legacy Initiative) ባለፉት ሦስት ዓመታት 18 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። ይህ መርሃ ግብር የኢትዮጵያን የደን ሽፋን ከማሻሻል ባሻገር ለምግብ ዋስትናና ለአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች አማራጭ መፍትሄ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባለፉት ዓመታት ስለተከናወኑት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች እና ስለዘንድሮው የችግኝ ተከላ ዘመቻ ባስተላለፉት መልዕክት፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የአየር ንብረት ለውጥን የምትቋቋም አረንጓዴ ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ዓላማ እንዳለው አስታውሰው፤ መርሃ ግብሩ እስካሁን በርካታ ውጤቶችን ማስመዝገቡን ገልጸዋል። በመርሃ ግብሩ የሦስት ዓመታት ትግበራ ወቅት በመላ ሀገሪቱ ከ20 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን በማሳተፍ 18 ቢሊዮን የሚጠጉ ችግኞች ተተክለዋል፤ ዓመታዊ የመጽደቅ ምጣኔውም ከ80 በመቶ በላይ ነው። ከ183ሺ በላይ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል።

ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም በአንድ ጀምበር 200 ሚሊዮን ችግኞች የመትከል ዕቅድ ተይዞ በዕለቱ፣ በ12 ሰዓታት ብቻ፣ 354 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ከእቅዱ በላይ ማሳካት ተችሏል። ሀገራዊ ምርጫ በተካሄደበት ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ደግሞ ኢትዮጵያውያን ድምፃቸውን ከመስጠታቸው በተጨማሪ በዕለቱ በችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ላይ ተሳትፈው የማይረሳ የዴሞክራሲና የአረንጓዴ አሻራቸውን አስቀምጠዋል።

ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለችግር መጋለጧን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ለዚህ ችግር ከተሰጡ ፈጣን የተግባር ምላሾች መካከል አንዱ መሆኑን ገልጸዋል። ‹‹በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ትግበራ የተከናወኑና በቀጣይም የሚከናወኑ ተግባራት የካርበን ልቀትን እንዲሁም የአየርና የውሃ ብክለትን ለመቀነስ፣ እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች ዝናብ እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የመሬት መንሸራተትና የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ ጉልህ ሚና እንደሚኖራቸው አንጠራጠርም›› ብለዋል።

የአረንጓዴ አሻራው አራተኛ ዙር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ‹‹አሻራችን ለትውልዳችን›› በሚል መሪ ቃል ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በይፋ ተጀምሯል። ከሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለተከላ የተዘጋጁበት የዘንድሮው መርሃ ግብር፣ በአራት ዓመታት ለማሳካት የታቀደው 20 ቢሊዮን ችግኞችን የመትከል እቅድ ከእቅዱ በላይ የሆነ አፈፃፀም እንዲያስመዘግብ ያስችላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አራተኛውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን በይፋ ባስጀመሩበት ወቅት ‹‹ላለፉት ሦስት ዓመታት በስኬት ሲከናወን የቆየውና ዘንድሮም የቀጠለው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ኢትዮጵያ ትልልቅ ነገሮችን መጀመር ብቻ ሳይሆን የምትጨርስ ሀገር እንደሆነች ለዓለም ያሳየችበት ነው›› ብለዋል። ‹‹በቀኝ እጃችን ልማታችንን በማስቀጠል በግራ እጃችን ደግሞ ጠላቶቻችንን በመዋጋት ሀገራችንን ለመለወጥ እንሠራለን›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፤ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት አንድ ሰው መቶ ችግኝ የመትከል መርሐ ግብር እንደሚጀመርና በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር አንዱ ትኩረት የተሰጠው አትክልትና ፍራፍሬ መትከል መሆኑንም ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹በአሮጌ አስተሳሰብና አተያይ ኢትዮጵያን የመሰለ ታላቅ አገር ማስቀጠል ያስቸግራል። የኢትዮጵያውያንን አመለካከት በማደስ ኢትዮጵያን ማደስ አለብን። ስለሆነም ሕጎችን፣ አሠራሮችን እያሻሻልን ነው፤ ቤቶች እያደስን ነው፤ የቆሙ ፕሮጀክቶችን በማፋጠን እየተጠናቀቁ ነው፤ ይህ በቂ ስላልሆነ ችግኞችን በመትከል ምድራችን እያደስን ነው›› በማለት ተናግረዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በበኩላቸው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ዓለምን ያስደመመ ሥራ መሰራቱን አስታውሰው፣ ለዚህ ዘመን ትውልድ የሚመጥን በበጎ መልኩ ሊወረሱ የሚችሉ ተግባራትን ማውረስ እንደሚገባ ገልጸዋል። የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብሩ ኢትዮጵያ ለስነ ምህዳር መጠበቅ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች እንደምትገኝ ማሳያ ስለመሆኑም ተናረግዋል።

በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ከተዘጋጁት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞች መካከል 52 በመቶ የሚሆኑት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሲሆኑ 47 በመቶው የደን ችግኞች መሆናቸውን የተናገሩት ደግሞ የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሑሴን ናቸው። ሚኒስትሩ እንዳሉት፣ ችግኞቹ የመሬት መራቆትን በመግታት፣ የአየር ንብረት ለውጥን በመቀነስ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። በችግኝ ተከላው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞች እየተለዩ እየተተከሉ እንደሆነም አቶ ዑመር ተናግረዋል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በርካታ ውጤቶች የተገኙበትና መልካም ተሞክሮዎች የተቀሰሙበት ተግባር ስለመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመስክሮለታል። በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ታደሰ ባለፉት ሦስት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የትግበራ ዓመታት በየዓመቱ ያስገኛቸው ብዙ መልካም ተሞክሮዎች እንዳሉ ይገልፃሉ። እንደርሳቸው ገለፃ፣ የፍራፍሬ ችግኞች ተከላ በየዓመቱ እያደገ መጥቷል። ዘንድሮ ደግሞ ካለፉት ሦስት ዓመታት በላቀ መልኩ ለፍራፍሬ ችግኞች ትኩረት ተሰጥቶ ለተከላ ዝግጅት ተደርጓል።

ኅብረተሰቡ ስለአረንጓዴ አሻራ ያለው ግንዛቤ እያደገ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት ያለው የማኅበረሰብ ግንዛቤ ከአራት ዓመታት በፊት ከነበረው በእጅጉ የተሻለ ነው። የግንዛቤው ማደግ የኅብረተሰቡ ችግኝ የመትከልና የመጠበቅ ባህሉና ጥረቱ እንዲጨምር ያደርጋል። ችግኝ መትከል እንደባህል እየተለመደ መጥቷል። የእነዚህ ቅንጅት ደግሞ ከችግኝ ተከላ መርሃ ግብሩ የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ እድል ይፈጥራል።

ለሀገር በቀል ዛፎች የተሰጠው ትኩረትም በየዓመቱ እያደገ መምጣቱ ሌላው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ውጤት ነው። ከመርሃ ግብሩ መጀመር በፊት በነበሩት ዓመታት ይተከሉ የነበሩት ችግረኞች የውጭ ዝርያ ያላቸውና በፍጥነት የሚደርሱ ችግኞች ነበሩ።

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን ከበጋ ወራት የሥነ አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ጋር አቀናጅቶ ማዝለቅ መቻሉም በመርሃ ግብሩ ትግበራ የተገኘ ውጤት ነው። የበጋ ወራት የሥነ አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ሲሰሩ በክረምት የሚከናወነው የችግኝ ተከላ ስራ ታሳቢ ተደርጎ መሰራቱ እና እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች ውሃን ለመሰነቅ የሚደረጉት ጥረቶች እየተሻሻሉ መምጣታቸው በመልካም ተሞክሮነት የሚጠቀሱ ናቸው።

በእርግጥ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ የተከናወነው ፍፁም ከችግሮች በፀዳ መልኩ እንዳልሆነ ይታወቃል። አቶ ተፈራ እንደሚናገሩት በመርሃ ግብሩ በመልካም ተሞክሮነት የተገኙት ውጤቶች እንከን አልባ ናቸው የሚባሉ ስላልሆኑ የእነርሱ ጉድለቶች በመርሃ ግብሩ ትግበራ ላይ እንዳጋጠሙ ችግሮችና የአፈፃፀም ክፍተቶች ተደርገው ይቆጠራሉ። ሀገር በቀል ዛፎችን የማዘጋጀትና የመትከል ስራው አሁንም ገና ብዙ የሚቀረው ተግባር ነው። የድህረ ተከላ ስራዎችም ከአፈፃፀም ክፍተቶች መካል የሚጠቀሱ ናቸው። ችግኞች ከተተከሉ በኋላ የሚከናወኑ አንዳንድ የድህረ ተከላ ተግባራት በአጥጋቢ ሁኔታ አለመከናወናቸው በችግኞች የመጽደቅ ምጣኔና በሚጠበቀው ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

‹‹በእርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የችግኝ የመጽደቅ ምጣኔ አመልካቾች እንደሚያሳዩት የችግኞች የመፅደቅ ደረጃ ከ70 ከመቶ በላይ ከሆነ የተሻለ አፈፃፀም እንደተመዘገበ ይቆጠራል። ባለፉት ሦስት ዓመታት በተከናወኑ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች የተመዘገበው የመጽደቅ ምጣኔ ደግሞ ከ80 በመቶ በላይ ነው። እኛ ግን ከዚህም በላይ እንዲጸድቅ ፍላጎት ስላለን እንጂ ባለፉት ሦስት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሮች የተመዘገበው የመፅደቅ መጠን ከዓለም አቀፍ መመዘኛ አንፃር ሲታይ ከፍተኛ ተደርጎ የሚወሰድ ነው›› ይላሉ።

የጥበቃ ስራ ከድህረ ተከላ ስራዎች የሚመደብ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ተፈራ፣ በዚህ የድህረ ተከላ ተግባር ረገድ በአንዳንድ ቦታዎች ለችግኞች የሚደረገው ጥበቃ በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ ከመርሃ ግብሩ ትግበራ ችግሮች መካከል አንዱ እንደሆነም ይናገራሉ።

ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም፣ በይፋ የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ አራተኛ ዙር የችግኝ ተከላ መርሃ



ፎቶ-ዳኜ አበራ

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ሰኔ 14 ቀን 2014 ዓ.ም የዘንድሮውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በይፋ አስጀምረዋል**

ግብር በአራት ዓመታት የችግኝ ተከላ ወቅቶች ለማሳካት የታቀደው 20 ቢሊዮን ችግኞችን የመትከል እቅድ ከእቅዱ በላይ እንዲሳካ ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል። በዚህኛው ዙር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከሰባት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለተከላ ተዘጋጅተዋል፤ የመትከያ ቦታ ዝግጅት መጠናቀቁም ተገልጿል።

ለተከላ ከተዘጋጁት ችግኞች ውስጥ ከሦስት ቢሊዮን በላይ የደን ችግኞች፣ ከሁለት ቢሊዮን በላይ ዘርፈ ብዙ ጥቅም የሚሰጡ የጥምር ደን ችግኞች፣ ከ500 ሚሊዮን በላይ የፍራፍሬ ችግኞች፣ 35 ሚሊዮን የቀርከሃና 800 ሚሊዮን ደግሞ ለእንስሳት መኖ ጥቅም የሚሰጡ ቁጥቋጦዎች እና ለከተማ ውበት የሚያጎናጽፉ ችግኞች መሆናቸውን የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ።

በዚህ መርሃ ግብር ከሚተከሉት ችግኞች መካከል ከግማሽ ቢሊዮን በላይ የሚሆኑት እንደ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ማንጎና አፕል ያሉ ለምግብነት የሚውሉ የፍራፍሬ ችግኞች መሆናቸው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ ኢትዮጵያን አረንጓዴ በማልበስ የደን ሽፋኗን ከመጨመር የተሻገረ ዓላማና ፋይዳ እንዳለው ዓይነተኛ ማሳያ ነው። መርሃ ግብሩ ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችን ማካተቱ ለምግብ ዋስትናም ሆነ ለግብይት አገልግሎት ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

አቶ ተፈራ ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የተዘጋጁት ችግኞች በብዛትም ሆነ በስብጥር ካለፉት ዓመታት የተሻሉ እንዲሆኑ ስለመደረጉ ይገልፃሉ። ‹‹ለአብነት ያህል ዘንድሮ ለተከላ የተዘጋጀው የፍራፍሬ ችግኝ ቁጥር ባለፉት መርሃ ግብሮች ከተተከሉት የፍራፍሬ ችግኞች የበለጠ ነው። የዛፍ ዝርያ ያላቸው ብዙ ዓይነት ችግኞችም ለተከላ ተዘጋጅተዋል። የደን፣ የቀርከሃ፣ ዘርፈ ብዙ ጥቅም የሚሰጡ፣ የከተማ ውበት ማስጠበቂያ፣ የመኖና ሌሎች ችግኞች ተዘጋጅተዋል። የተተከሉ ችግኞች እንዳይፀድቁ አንዱ መሰናክል ልቅ ግጦሽ ነው።

ልቅ ግጦሽን ማስቀረት የሚቻለው ለእንስሳት ቀለብ የሚሆን ምግብ ማቅረብ ሲቻል በመሆኑ ለመኖ ችግኞች ትኩረት ተሰጥቶ ለተከላ እንዲዘጋጁ ተደርገዋል›› በማለት ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪም የመንግሥት መዋቅርን በመጠቀም ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ስለመከናወናቸው፣ ከመንግሥት የተመደበው በጀት በአግባቡ ለችግኝና ለተከላ ቦታዎች ዝግጅት እንዲውል ስለመደረጉ እንዲሁም የችግኝ ተከላውን ውጤታማ ለማድረግ ከክልሎች ጋር በቅንጅት ስለመሰራቱም ያብራራሉ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ በቂ ዝግጅት መደረጉን ቀደም ብሎ አስታውቆ ነበር። ቋሚ ኮሚቴው ከዚህ ቀደም የተከናወኑትን የአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች ውጤታማነት መገምገሙንና ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ የተከናወኑት የዝግጅት ተግባራት ጥሩ አፈፃፀም እንደነበራቸው ገልጿል።

የግብርና ሚኒስቴርም ለዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በመንግሥት ችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች፣ በማህበር በተደራጁ ወጣቶች እና በግለሰቦች የተዘጋጁ በቂ ችግኞች ለተከላ ዝግጁ እንደተደረጉ መግለፁ ይታወሳል። እንደሚኒስቴሩ መረጃዎች የዘንድሮው መርሃ ግብር የተጋለጡ መሬቶችንና ከዚህ ቀደም ችግኝ ተተክሎባቸው ውጤት ያላመጡ መሬቶች ላይ በድጋሚ በመትከል እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ አዳዲስ መሬቶችን እየፈለጉ በመትከል የሚተገበር ይሆናል። የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ሲጀመር 27 የነበሩት የችግኝ ጣቢያዎች በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው 121 ሺህ ደርሷል።

ችግኝ መትከል ብቻ ውጤት እንደማያስገኝ በኅብረተሰቡም የታወቀ፣ በመንግሥት አካላትም ተደጋግሞ የሚነገር ሃሳብ ነው። እንክብካቤ ትልቅ ትኩረት የሚሻ ተግባር እንደሆነ ማብራሪያ የሚፈልግ ጉዳይ አይደለም። ‹‹ችግኝ መትከል በራሱ ግብ አይደለም›› የሚሉት አቶ ተፈራ፣ ‹‹ግብ ሊሆን የሚችለው የተተከሉት ችግኞች ፀድቀውና አድገው ማገዶ፣ የቤት መስሪያ መሆን ሲችሉ፣ የሚፈለገውን ምርት ሲሰጡና ከምርቱ ተጠቃሚ መሆን ሲቻል በአጠቃላይ ችግኞቹ አድገው በግለሰብም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ የተተከሉበትን ዓላማ ማሳካት ሲችሉ ነው። ስለሆነም የድህረ ተከላ ተግባራትን በትልቅ ትኩረት ማከናወን ይገባል›› ይላሉ። የድህረ ተከላ ስራዎች በየዓመቱ መሻሻሎችን እያሳዩ ቢሆንም ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየተፈተነች የመሆኗ እውነታ በአረንጓዴ አሻራ በንቃት የመሳተፍ ተግባር ለኢትዮጵያውያን አማራጭ ሳይሆን ግዴታ እንዲሆን ያደርገዋል። ኢትዮጵያውያን ‹‹ችግኝን ተክሎ አለመንከባከብ ማለት ወልዶ መጣል ማለት ነው›› ሲሉ ይደመጣሉ። እውነት ነው፤ችግኝ እንክብካቤና ክትትል ስለሚፈልግ ችግኝን በልጅ፣ የተከለውን ችግኝ አለመንከባከብን ደግሞ ልጅን ወልዶ ከመጣል ጋር ማነፃፀር ስህተት አይሆንም። ስለሆነም በችግኝ ተከላው በንቃት መሳተፍና የተተከሉ ችግኞችንም በመንከባከብ በአሁኑ ወቅት ዓለምን ለረሀብ፣ ለስደትና ለመከራ የዳረጋትን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም የሚደረገውን ጥረት በብርቱ ማገዝ ከኢትዮጵያውያን የሚጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ተስፋ የተጣለበት ዳግም ፈተና እና ዝግጅቱ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

በ 2013 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ፈተና የወሰዱ ተማሪዎች በሁለት ዙር የተፈተኑ ሲሆን፤ በሁለቱም ጊዜ የተለያየ ችግር አጋጥሞ እንደነበር ይታወሳል። በተለይም የሁለተኛው ዙር ፈተና በጦርነቱ አካባቢ ለሚኖሩ ተማሪዎች ትልቅ ተግዳሮት ነበር። ምክንያቱም ተረጋግተው ባለመፈተናቸውና የደረሰባቸው የስነ ልቦና ጉዳት ውጤታቸው ላይ ጥላ በማጥላቱ። በዚህም ውጤት ይፋ በተደረገ ጊዜ በስፋት የችግሩ ሰለባ የነበሩ አካባቢ ብዙ ጥያቄ ሲያነሱ ነበር።

በተለይም በሰሜኑ ጦርነት ተጎጂ ከነበረው ክልል መካከል የአማራ ክልል ውጤት ብዙዎችን ያሳዘነና ጥያቄ ያስነሳ እንደነበረም ታይቷል። በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ተማሪዎች ዳግም ፈተናውን እንዲወስዱ አቅጣጫ አስቀምጧል። ለአማራ ክልል ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ግጭት ለነበረባቸው ክልሎች ተስፋ ሰጪ እንደሆነም ይነገርለታል። ሆኖም በሚገባ ከተዘጋጁበት ብቻ ነው እድሉ ለስኬት የሚያበቃው።

ይህ እድል ከተሰጣቸው መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ የሕዝብ ግንኙነትና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ቢያዝን ሲናገሩ፤ አካባቢው በወረራና በጦርነት ውስጥ በመሆኑ የክልሉ ሕዝብ ዋና ትኩረቱን አድርጎ የነበረው ራሱን ማዳንና መታገል ላይ ነበር። ተማሪዎችም የዚሁ አካል ነበሩ። ይህ ደግሞ ብዙ ጫና አሳድሯል። ስለሆነም በስነልቦና ተዘጋጅተው መፈተን አልቻሉም። ውጤቱ ያሰቡትን ያህል እንዳይሆንም ያደረገው ይህ ነው።

ትምህርት ሚኒስቴር በሰጠው እድል ለመጠቀም የችግሩን አሳሳቢነትና ውስብስብነት ለባለድርሻ አካላት የማሳወቅ ሥራ እንደተሠራ የጠቆሙት አቶ ጌታቸው፤ ሁሉም ትምህርት ቤት አውቆ እንዲሠራበትም አቅጣጫ ወርዷል። ውሳኔዎች ከተላለፈባቸው መካከልም ቅድሚያ የተሰጠው ውጤት ማሻሻልን የተመለከተው ጉዳይ ሲሆን፤ ጎን ለጎን የስነልቦና የምክር አገልግሎትም እንደሚደረግ አንስተዋል።

የውጤት ማሻሻያ ተብለው የተወሰዱ ውሳኔዎች ምንም እንኳን ተማሪዎቹ በብዙ መንገድ ትምህርቱን የሸፈኑና የፈተናውን ሁኔታ የተለማመዱት ቢሆንም፤ ተረጋግተው አላደረጉትምና ያውቁታል ለማለት ያስቸግራል። ስለሆነም ዳግም ሁሉንም መደበኛ ትምህርት የሚከታተሉበትን ዕድልመፍጠር አስፈልጓል። ከመደበኛ ተፈታኞች ጋር አብረው እንዲማሩና ሞዴል ጭምር እንዲወስዱም ውሳኔ ተላልፏል። በተጨማሪ ቅዳሜና እሁድ ሳይቀር እንዲማሩ የሚደረግበት ሁኔታ ተመቻችቷል። የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል) ክላስም እንዲሁ ከመደበኛው ተማሪ እኩል እንዲሳተፉም መደረጉን አስረድተዋል።

የመጽሐፍ እጥረት የሚያጋጥም ሲሆን፤ ተማሪዎች ዋይ ፋይ ባለባቸው ቦታዎች ላይ እየገቡ መጽሐፍትንና የተለያዩ ነገሮችን በማውረድ የሚያጠኑበትን አጋጣሚ ክፍት መደረጉን ያነሱት ኃላፊው፤ ቤተ መጽሐፍትም እንደፍላጎታቸው የሚጠቀሙበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል ብለዋል። በትምህርት ሥርዓቱ ከሰኔ 30 በኋላ ትምህርት ያበቃል። ሆኖም ዳግም ተፈታኞችም ሆኑ መደበኛ ተፈታኞች ሐምሌና ነሐሴ መዘናጋት እንዳይገጥማቸው ባለበት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉም እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ጌታቸው፤ ምን ምን ነገሮች መሟላት እንዳለባቸው ከአሁኑ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

> **ለተማሪዎቹ ውጤት መላሸቅ አንዳንድ ብልሹ አሠራሮች አሁንም ስለሚታዩ ይህንን ማረም ያስፈልጋል፤ ካልሆነ ግን ሰዎች በተለያየ መንገድ ያለእውቀታቸው ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገባሉ፤ መግባት የነበረባቸው ጎበዝ ተማሪዎች ይቀራሉ**

ይህንን የፈተና ጊዜ ለማለፍ መምህራን ከምንም በላይ እየተጉ እንደሆነ የገለጹት አቶ ጌታቸው፤ የዘንድሮ ውጤት ተማሪውን ብቻ ሳይሆን የክልሉን ነዋሪ ጭምር ልብ የሰበረ ነው። በተለይ መምህሩ በእጅጉ አዝኗል። በዚህም ቁጭታቸውን ለመወጣት ከምንም በላይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በማስተማር ላይ ናቸው። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የተለያዩ ወርክ ሾቶችን ያሠሯቸዋል። ተማሪዎች በሚመቻቸው ልክ ቀርበዋቸው ይደግፏቸዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በሚፈለገው መጠን እንዲዘጋጁ እያደረጋቸው እንደሆነ ይናገራሉ።

ሥራውን ሲያከናውኑ መጀመሪያ የተማሪዎች ውጤት በአግባቡ ተፈትሾ ወዳቂው እንዲታይ ማድረግ፣ ከዚያም ባሻገር ጎበዝ ተማሪዎች ውጤታቸው ታይቶ ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድል እንዲያገኙ ማስቻልና በመጨረሻም ቀሪዎቹ ዳግም እንዲፈተኑ ማገዝ የሚሉ ሲሆኑ፤ ሁሉም በተደረጉት ውይይቶችና ትግሎች ውሳኔዎች ተላልፎባቸዋል። ምክንያቱም ክልሉ በግጭት ረጅም ጊዜን በማሳለፉ ችግር ገጥሟል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ በውሳኔው ልክ ትግበራው ሙሉ ለሙሉ እየሄደ ነው ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ሁኔታዎች ወደውሳኔው ለመግባት ላያስችሉ ይችላሉ። ለአብነት የክፍል ጥበት ካለ ቅድሚያ የሚሰጠው ለመደበኞቹ ተማሪዎች ይሆናል። እናም ዳግም ተፈታኞች እድሉን ላያገኙ ይችላሉ። በተመሳሳይ የመጽሐፍት እጥረትና መሰል ነገሮች ፈተና ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን የተለዩ አማራጮችን ከመጠቀም ወደኋላ አልተባለም። ለምሳሌ፡- ፈረቃ እያስተካከሉና ጊዜያዊ መማሪያ ክፍል እየገነቡ ማገዙ አንዱ ነው። የመጽሐፍት እጥረትን ደግሞ ቤተመጽሐፍት ገብተው በጋራ እንዲጠቀሙ ማስቻል መፍትሔ ተደርጓል።

ከፍተኛ ግጭት በነበረበት በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ ፍላቂት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማረው ዳግም ተፈታኝ ሳሙኤል ጸጋዬ እንደሚለው አቅጣጫው በተለይም እነሱ ባሉበት ወረዳ ላይ ሙሉ በሙሉ እየተተገበረ አይደለም፣

ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቻሉትን ያህል እያደረጉ እንደሚገኙ የሚያነሳው ሳሙኤል፤ በአቅራቢያቸው ያሉ ትምህርት ቤቶች ላይም ተግባሩ እየተከናወነ ነው ለማለት እንደሚቸገር ይገልጻል።

የዘንድሮ ፈተና ባልጠበቅነውና ባልተረጋጋንበት ሁኔታ እንድንፈተን መሆኑ በውጤታችንም ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖን አሳድሯል የሚለው ተማሪ ሳሙኤል አሁንም ለተማሪዎች የተሰጡ የዳግም ፈተና እድሎች በትክክል መሬት ወርደው ተግባራዊ ቢሆኑ ውጤቱ እንደሚሻሻል የመንግስት ጥረትም ውጤት እንደሚያመጣ ነው የሚናገረው፡፡

እርሱ ያመጣው ውጤት 407 ነው ጎበዝና ፈተናውን በአግባቡ እንደሠራው ስለሚረዳ ዳግም እንዲታረምለት ጠይቆ እንደነበር ገልጾ ይህም ምላሽ አለማግኘቱ ቅሬታ እንደፈጠረበት ያብራራል ፡፡

እርሱ እንደሚለው፤ ለተማሪዎቹ ውጤት መላሸቅ አንዳንድ ብልሹ አሠራሮች አሁንም ስለሚታዩ ይህንን ማረም ያስፈልጋል፤ ካልሆነ ግን ሰዎች በተለያየ መንገድ ያለእውቀታቸው ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይገባሉ፤ መግባት የነበረባቸው ጎበዝ ተማሪዎች ይቀራሉ፤ ይህ ደግሞ ለሀገርም ኪሳራ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ባሉት ሂደቶችም ሊታሰብበት እንደሚገባ አብራርቷል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ በበኩላቸው፤ እንደ ክልል የተሰጠው እድል ብዙ ነገር ይዞ ይመጣል። ኦሮሚያ ክልልም ብዙ የተጠቀመበት ነው። ወደ 21 ሺህ ከሚጠጉት ተማሪዎች ውስጥ ትምህርት ሚኒስቴር በሰጠው እድል ሦስት ሺህ ያህሉ ተጠቃሚ ሆነዋል። አሁንም የቀሩት ተማሪዎችን ብዙ ቢሆኑም ለማገዝ ይሞከራል ብለዋል።

በክልሉ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዙ ናቸው። በሀገሪቱ ከሚፈተነው ተማሪ ውስጥ 42 በመቶውን ይይዛሉ። ስለሆነም ዳግም ተፈታኞችን በመደበኛው ልክ ለማገዝ አዳጋች ነው የሚሉት ዶክተር ቶላ፤ በተቻለ መጠን አንዳንድ እድሎችን ለመስጠት እንደሚሠራ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ቤተመጽሐፍትን እንዲጠቀሙ፣የማጠናከሪያ (ቲቶሪያል) ትምህርት ላይ እንዲሳተፉ ፣እንዲሁም ተማሪዎቹ በራሳቸው እንዲዘጋጁ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ፣ ይህ በመንግሥት የተመቻቸው እድል ለሁሉም ይሠራ ዘንድ እስከታች ተወርዶ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ግጭት ያለባቸው ቦታዎች ተብለው የተለዩና በሁለተኛ ዙር የተፈተኑት ተማሪዎች ወደ 54 ሺህ የሚደርሱ ሲሆኑ፤ ከትምህርት ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሠረት በ43 የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በአጠቃላይ 152ሺ 144 ተማሪዎች እንዲማሩ ተደርጓል። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍ ያለ ነው። ነገር ግን ሚኒስቴሩ የጸጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የፈተና ውጤትን ለመለየት ዳግም ፈተና ለወደቁት እንዲሰጥ ተገዷል።

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ፤ ተማሪዎች ይህ እድል ሲሰጣቸው አንድም አዎንታዊ ሌላም አሉታዊ ነገር ይገጥማቸዋል። እንደቢሮ ግን የሚፈለገው አዎንታዊው እንዲሰፋ ነውና ለዚህ የሚያግዝ ሥራ እየተሠራ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ካልተጠቀሙት እድሉ በራሱ ይዞ የሚመጣው ነገር የለም። ስለሆነም በሆነው ነገር ሳይቆዝሙ እድሉን መጠቀሙ ላይ ትኩረታቸውን ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበዋል። መምህራን፣ቤተሰብ ፣ የክልሉ ማኅበረሰብም ለዚህ ሥራ ውጤታማነት ተሳትፎን እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ዶክተር ቶላ በበኩላቸው፤ ይህ እድል መቼም ያልሆነና ወደፊትም ሊፈጠር የማይችል በመሆኑ ተማሪዎች ከመዘናጋት ወጥተው ቤተ መጽሐፍትንና የማጠናከሪያ ትምህርት (ቲቶሪያል) ላይ ባለመቅረት የራሳቸውን ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸውም ተናግረዋል። ይህ ደግሞ የማስታወስና የማንበብ ክህሎታቸው በአለበት እንዲቀጥል ያደርጋቸዋል። ለውጤታማነታቸው እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አምነው ሊጠቀሙበት እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

እድሉ በቀላሉ የመጣ እንዳልሆነ የሚናገሩት አቶ ጌታቸው፤ይህ ሥራ የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ ነው። በተለይም ተማሪዎች የተሰጣቸውን እድልና የሚደረግላቸውን ድጋፍ በቸልታ ሊያዩት አይገባም።

‹‹በግጭት አካባቢ የነበሩ ተፈታኞች በተለይም ጎበዝ የሚባሉት ውጤታቸው ዳግም እንዲታይ እንኳን አልተደረገም። ስለሆነም በሁሉም መንገድ የተጎዳ ተማሪ አድርጎናል›› የሚለው ተማሪ ሳሙኤል፤ የተሰጠው እድል መልካም ቢሆንም አሁንም ጥንቃቄ ያሻዋል። መንግሥት ይህንን አይቶ ከመቼውም በላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል። የሚሰጣቸውን እድሎች ታች ወርዶ መተግበራቸውን ማየት፤ የእድሉን አሰጣጥ ግልጽ ማድረግ፤ ሁሉንም ለመጥቀም መሞከር ያስፈልጋል ብሏል ፡፡

ይህ እድል የተሰጣቸው ተማሪዎችም ቢሆኑ በስነልቦናም ሆነ በትምህርት መታገዝ አለባቸው የሚለው ተማሪው፤ ተማሪዎቹም ይህ እድል የማይደገም ነውና በአግባቡ ተስፋ ሳይቆርጡ መጠቀም እንዳለባቸው ይመክራል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹በጊምቢ በንጹሓን ዜጎች ላይ የተፈፀመው ዘግናኝ ድርጊት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳዘነ ነው፤ ድርጊቱ በትክክል ተጣርቶ በአጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ መወሰድ አለበት››

**የቀድሞ ሠራዊት ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ**

ምሕረት ሞገስ

ብርጋዴር ጄኔራል ዋሲሁን ንጋቱ የተወለዱት በቀድሞ የወለጋ ጠቅላይ ግዛት በሆሮ ጉዱሩ አውራጃ በ1933 ዓ.ም.ነበር። የአንደኛ እና የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው በትውልድ አካባቢያቸው በወለጋ አጠናቅቀዋል። በ1953 ዓ.ም. የሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤትን ተቀላቅለው ብቁ የመከላከያ ሰራዊት የሚያደርጋቸውን ወታደራዊ ትምህርት ቀስመዋል። ብርጋዴር ጄኔራሉ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የታንከኛ መሠረታዊ ትምህርት፣ ከፍተኛ የውጊያ መረጃ ትምህርት፣ የአውሮፕላን የአየር ቅኝት፣ የአየር በረራ ጠለፋ፣ ከፍተኛ የታንክ ትምህርት ተምረዋል።

በኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር የቀድሞ ሠራዊት ውስጥ በተለያዩ የጦር ግንባሮችና የጦር ክፍሎች ለ30 ዓመታት ሀገራቸውን በማገልገል ወታደራዊ ግዳጃቸውን በብቃትና በትጋት እና በታማኝነት የተወጡ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንንም ናቸው። በተጨማሪ በወታደር አዛዥነታቸው ዘመን ከሕዝብ ጋር በቅርበት በመሆን በአካባቢ ሠላም ዙሪያ ከሽማግሌዎች ጋር በመነጋገር መረጋጋትን በመፍጠር ይታወቃሉ። በአማራ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች ፣ በትግራይም ሆነ በሌሎች ክልሎች ተዘዋውረው የወታደር አዛዥ ሆነው አገራቸውን አገልግለዋል። ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን የወቅቱን የፀጥታ እና የደህንነት ሁኔታን በተመለከተ፤ በተለይ በጋምቤላም ሆነ በምዕራብ ኦሮሚያ ጊምቢ ወረዳ ስለተፈፀመው ድርጊት ምን ይላሉ? ምን መደረግ አለበት ? በማለት አነጋግረናቸው እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ያለውን የፀጥታ እና የደህንነት ሁኔታ በሚመለከት ምን ይላሉ? ጋምቤላም ሆነ ኦሮሚያ ክልል ላይ ስለተፈፀመው ጥቃት ያልዎትን አስተያየት ይግለፁልኝ ?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** የወቅቱ የኢትዮጵያ የሰላም እጦት ሲነሳ በዋናነት ይነሳል። ሕወሓት በሰላማዊ መንገድ ሁሉን ነገር መፍታት ሲቻል ጦርነት ከፍቷል። መንግሥት ለሰላም የሰጠውን ትኩረት በመናቅ ጦርነት በመክፈቱ ብዙ ጥፋት አስከትሏል። ይህ እጅግ በጣም ያሳዝናል። መንግሥት ፈልጎ ጦርነት ውስጥ አልገባም፤ መንግሥትን ያስገደደው የሽብር ቡድኑ ራሱ ሕወሓት ነው። አሁን ጦርነቱ ከተጀመረ አንድ ዓመት ከስድስት ወር አልፎታል።

ቡድኑ ሀገሪቱን ፈፅሞ አላስፈላጊ ጦርነት ውስጥ የከተታት፤ አቅምን ባለማወቅ እና በእብሪት ነው። በእርግጥ የትግራይ ሕዝብ ተበድሏል ከሚል ቁጭት እና ለትግራይ ሕዝብ ለመከላከል አይደለም። የትግራይ ሕዝብ ተበድሎ ቢሆን እንኳ ጦርነት ለመንግሥትም ሆነ ለተቃዋሚም ለማንም በፍፁም አይጠቅምም። ጦርነት እልቂት ነው። ኢኮኖሚን የሚያወድም ነው። ከጦርነት በፊት ቀድሞ መነጋገር ይሻል ነበር።

በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እየተፈፀመ ያለው ጥፋት አሰቃቂ ነው። መንግሥት ሆነ ብሎ ሕዝብን የሚበድል አይመስለኝም። በምዕራብ ኦሮሚያ በጊምቢ ወረዳ የተፈፀመው የሰው ልጅ ካላበደ በስተቀር በገዛ ወገኑ ላይ እንዲህ አይነት ግፍ ይፈፅማል ብሎ ለመገመት የሚያዳግት ነው። ሰውን አልፎ ተርፎ ሕፃናትን መግደል እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው። ሁሉም ሰላምን የሚወድ ኢትዮጵያዊ በሙሉ በዚህ ተግባር ማዘኑ አይቀርም።



ፎቶ፡- ከደክመንት

እኔም እንደሁሉም ኢትዮጵያዊ በዚህ ተግባር እጅግ በጣም አዝኛለሁ። በእኔ እምነት ይህ ድርጊት የተፈፀመው፤ መንግሥት ተከታትሎ በየወቅቱ እርምጃ ባለመውሰዱ ነው፡፡

የወታደር የጥቃት ዒላማዎች አሉ። ከዛ ውጪ የድሃን ቤት ማቃጠል እና ድሃን መግደል ለምን? ተነጋግሮ መግባባት ባይቻል እንኳን ወታደራዊ ዒላማን መጠቀም ሲቻል ሰላማዊ ሰዎችን ዒላማ ማድረግ ትልቅ ጥፋት ነው። ይህ ድርጊት በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ታይቷል። መንግሥት ትዕግስት አድርጓል።ነገር ግን ትዕግስትም ወሰን አለው። የችኮላ ውሳኔ ሳይሆን በተጨባጭ ማስረጃ የተገኘባቸው ላይ መንግሥት የማያዳግም እርምጃ መውሰድ አለበት።

መንግሥት ጥንቃቄ አድርጎ የድርጊቱ ፈፃሚዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ካልቻለ ድርጊቱ ይቀጥላል።

‹‹ትምህርት መስጠት ተገቢ ነው›› ይባላል። አጥፊዎች ቢሆኑም በእርግጥ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። ነገር ግን ትምህርት ብቻ ሳይሆን ማንኛውም የሰው ልጅ ይፈራል። ሆን ብሎ ቀይ መስመርን ያለፈ ካለ፤ መንግሥት ማስረጃ አስቀርቦ እርምጃ መውሰድ አለበት። ሻሸመኔ ላይ ተዘቅዝቆ ሰው ተሰቀለ። የሰቀሉት ላይ ምን እርምጃ ተወሰደ? አይታወቅም። በደቡብ በኩል አንድ ሰው ሚስቱን በጭካኔ በጩቤ ገድሏል ተብሎ ሞት እንደተፈረደበት ሰምቻለሁ። ሌሎች ላይም ወንጀል እየፈፀሙ ያሉ ቡድኖች ላይም እርምጃ በወቅቱ መወሰድ አለበት። የተፈረደባቸው ፍርድም ሊታወቅ ይገባል።

ማንም ሰው ከሕግ በላይ ሊሆን አይችልም። መንግሥት ሕግ ሲያስከብር ደግሞ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሃይማኖት መሪዎችም ተገቢውን ትምህርት በመስጠት ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዳኞችን ሌባ ናቸው ብለዋል። መስረቅ ተገቢ ባይሆንም፤ ግድየለም ብሎ ማለፍ ይቻላል። በዚህ ጊዜ ስርቆትን ማለፍ ይችላል።ሰው በተጨባጭ የገደለ ግን በዛው በገደለበት ቦታ ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል።ገዳዮች በተቃራኒው እንደሐረር ሰንጋ ታስረው መቀለብ የለባቸውም።በሶስት ምስክሮች ተረጋግጦ፤ በሶስት ዳኞች ተጣርቶ ከተፈረደ፤ እርምጃ መውሰድ የግድ ነው፡፡

በእኔ እምነት ከዚህ በኋላ የመንግሥት ትዕግስት መሰበር አለበት።ሰው የገደለ፤ ሰው ላይ ግፍ የፈፀመ ማንኛውም ሰው ላይ እርምጃ ካልተወሰደ በምንም መልኩ መንግሥትን መደገፍ ያስቸግራል።በጊምቢ በንጹሐን ዜጎች ላይ የተፈፀመው ዘግናኝ ድርጊት የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳዘነ ነው።በትክክል ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ መወሰድ አለበት ብዬ አምናለሁ።ይህንንም በተደጋጋሚ እናገራለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በምዕራብ ኦሮሚያ ዞን በጊምቢ ወረዳ የተፈፀመውን ጥቃት ሲያስቡ፤ የጋምቤላውም ሆነ ሌላውን ሲያዩ የእነዚህ ጥፋት ፈፃሚዎች ዓላማ እና ፍላጎት ምንድን ነው ብለው ይገምታሉ?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** በእውነቱ እንደሚመስለኝ እነዚህ ሰዎች እያሉ ያሉት ‹‹ስልጣን እንፈልጋለን ነው፡፡›› ነገር ግን ስልጣን ሰው እየገደሉ የሚገኝ አይደለም።ይሔ ድርጊታቸው ሕዝብንም መንግሥትንም የናቁ መሆኑን የሚያሳይ ነው።‹‹ያለእኛ ለኢትዮጵያ የሚያስብ የለም፤ ትክክለኛ እኛ ብቻ ነን›› ይላሉ።ድርጊታቸው አረመኔያዊ ነው።ይህ አምባገነንነታቸው በሥርዓት በሕግ መስተካከል አለበት።ለኦሮሞ ወደ 47 ዓመታት ታግለናል ያሉት እንኳ አያዋጣንም ብለዋል።ከጦርነትም ሆነ ከሽምቅ ውጊያ ራሳቸውን ወደ ሰላም ጎዳና መርተዋል።

አማራ ምን አደረገ? በአማራ አካባቢ ለብዙ ጊዜ ኖሬያለሁ። አሁን ደግሞ ስልጣን ላይ የወጣው መንግሥት በሕዝብ የተመረጠ ነው። በሰላም መኖር ሲቻል እንዴት ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊን ይገድላል? ሸኔም ሆነ ሕወሓት ኢትዮጵያውያን ናቸው።ኢትዮጵያን ለመግዛት የመጣው ጠላት ፋሺስት እንኳን የኢትዮጵያን ሕግ ካከበረ የመኖር መብት አለው። በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ አማራዎች በመኖራቸው መገደል የለባቸውም። ሕግ እስካከበሩ ድረስ የመኖር መብት አላቸው። ከዚህ ውጣ ብሎ የመግደል ስልጣን ለማንም አልተሰጠም። ይሔ መንግሥትን መናቅ ነው።ማንም ሰው መሞት አይፈልግም። እርምጃ ከተወሰደ ደግሞ መቆጣጠር ይቻላል። ይህንን ማድረጋቸው በትክክል ከተረጋገጠ ደጋግሜ እንደተናገርኩት እርምጃ ሲወሰድ ሌላው ይፈራል።

አማራ ምን አደረገ? አማራ ገዢ መደብ ነበረ ይባላል። ያ አልፏል። አሁን የአማራም ሆነ የኦሮሞ አምባገነን መኖር የለበትም። ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ሁሉም እኩል እንዲሆን ማድረግ አለበት። ይህ መቆም የሚችለው ወንጀለኞች ላይ አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ሲቻል ነው። በዚህ ከቀጠለ አስቸጋሪ ነው። አሁንም ጥፋት እንደአሸን እየፈላ ነው። መንግሥት በየኬላው ወታደር ማቆም አይችልም።ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ነገር እንዳይደረግ መንገር ማስረዳት፤ እንዳይደገም እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።እኔ ኮር አዛዥ ሆኜ አማራ ክልል ባህርዳር ለብዙ ጊዜ ቆይቻለሁ። እዚህ አትኑር ውጣ ያለኝ የለም።

መንግሥት ለሕወሓትም ሆነ ለሸኔ ለሁሉም የሠላም ጥሪ አቅርቧል። ነገር ግን አልተቀበሉትም። ይህም ቢሆን በተደጋጋሚ እታች ድረስ በመውረድ በሚገባቸው ቋንቋ ሊነገራቸው ይገባል። ስለሰላም መስበክ እና ማስረዳት ያስፈልጋል። ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት የሽብር ቡድኑን ሕወሓትን አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ የመጀመሪያውን ዙር ጨርሷል። አሁንም የጦርነት ዝግጅት እያደረጉ መሆኑ እየተነገረ ነው። ነገር ግን ጦርነት አይጠቅምም። ጥፋት ነው። የሚጠቅመው በሰላማዊ መንገድ ችግርን መፍታት ነው። ማስተማር ይጠይቃል። አባገዳዎችን እና ሽማግሌዎችን በመያዝ በየጎሳው በሚገባቸው ቋንቋ ማስተማር የግድ ነው። አሁንም በከተማም ሆነ በገጠር የሰላም ዘመቻ መታወጅ አለበት። እኛም አስራ አንደኛ ክፍል ሆነን ማርክሲስት ሌኒንስት እንማር ነበር። ማንንም በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለውን ስለሰላም ማስተማር ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- አደረጃጀቶች ላይ ችግር ካለስ መታየት የለበትም? በተለይ ቀድሞ መረጃ ካለ መጠበቅ እና መጠንቀቅ የነበረበት አካል ጥንቃቄ ሲያደርግ አይገባም?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** ይገባል! ።እዛ አካባቢ ያሉ ታጣቂዎች፣ ልዩ ኃይሎቹም ሆኑ ሌሎቹ ምልክት ካዩ መጠበቅ አለባቸው። ያለበለዚያ ጥቃት ሊደርስ መሆኑ እየታወቀ በቸልተኝነት ድርጊቱ ከተፈፀመ፤ እያወቁ ተገቢውን ጥንቃቄ ያላደረጉትም ጭምር ተጠያቂ መሆን አለባቸው። ቢጠነቀቁ ኖሮ ይህ ሁሉ እልቂት አይደርስም ነበር። እያንዳንዱ ኃላፊነት ያለበት መጠየቅ አለበት።

ድንበር ላይ የሚደረግ ጦርነት ቀላል ነው። የሽምቅ ውጊያ እና የከተማ ውጊያ አስቸጋሪ ነው። ጠላት እና ደጋፊ አይለይም። የጫካ እና የበረሃ ውጊያም ያስቸግራል። የእነኚህም ጥፋት የእርስ በእርስ በመሆኑ እርግጥ ያስቸግራል። ነገር ግን እነዚህ እንደጠላት ጦር መታየት የለባቸውም ፤ ሽፍቶች ናቸው። እንኳን ወገን መሳሪያ ያልያዘ ንፁህ ዜጋ ቀርቶ፤ ጠላት እንኳ እጁን ካወጣ ተማርኬያለሁ ካለ አይገደልም። እነዚህ አጥፊዎች ጠላት እንኳን የማይፈፅመው የንቀት ተግባር በገዛ ወገን ላይ ፈፅመዋል። የሚታየው ቸልተኝነትም ትክክል አይደለም።

ይህንን ድርጊት ፈፃሚዎች እነ ሸኔ አሰልጥነው እና አስተምረው ትምህርት ቤት አስመረቁ ይባላል።

# ወቅታዊ

ግብር እያስገበሩ እንደሆነም ይነገራል። ይህንን ሁሉ ሲፈፅሙ የሚተባበራቸው መዋቅር አለ ማለት ነው። የኦሮሚያ ግዛት ሰፊ ቢሆንም፤ ይህ ሁሉ ሲሆን እንዴት ዝም ይባላል? ሽፍታን ለመደምሰስ፣ አውሮፕላንም ሆነ መድፍ እንዲሁም ታንክም ሆነ ትልቅ መሣሪያ አያስፈልግም። አሰሳ አድርጎ መርምሮ አጣርቶ ማጠናቀቅ ይቻላል።

ኦሮሞ እንኳን ለራሱ ለኢትዮጵያ የሚሆን የዴሞክራሲ ሥርዓት አለው። አስመሮም ለገሰ የሚባል የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ የገዳ ስርዓት 200 ዓመታትን ፈጅቷል ከሚባለው የአሜሪካ የዴሞክራሲ ሥርዓት የተሻለ መሆኑን አጥንቶ አረጋግጧል። በዚሁ ጥናቱ ሶስተኛ ዲግሪውን አግኝቷል። ሰላም ለማስፈን የኢትዮጵያ ባህል ራሱ ምቹ ነው። ሽምግልና አለ። ፍርድ ይሰጣሉ። ስለዚህ በሀገር ላይ ሰላምን ለማስፈን ያለውን ባህል መጠቀም ይቻላል።

በሌላ በኩል የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይቀሩ ከሕግ በላይ አይደሉም፤ አመራርነት በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ የራስን ጣቶች መቀሰርን ያስገድዳል።መሪ ስትሆን እያንዳንዱን ነገር መቆጣጠር ይገባል። በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆኖ ይህንን አሰቃቂ ድርጊት የሚፈፅሙትን የሚረዳ መኖር የለበትም።በመንግስት መዋቅር ውስጥ ሆነው ይህንን የሚያደርጉት ምን ለማግኘት ነው? ማንም ቢሆን በኦሮሚያ የኦሮሚያን ባህል ጠብቆ መኖር ይችላል። ኢትዮጵያኖች አሜሪካ ሔደው ይማራሉ፤ ይኖራሉ። እኔም አሜሪካን ሄጄ ሁለት ዩኒቨርስቲዎች ገብቼ ተምሬያለሁ። ውጡ እናንተ የሚል የለም። ኢትዮጵያኖች አሜሪካን እየኖሩ በገዛ አገራቸው ለመኖር እንዴት ይከለከላሉ? ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወለጋ፣ ሀረር ... የትም ቦታ ላይ የመኖር መብት አለው። ነገር ግን የመንግሥት መላላት እና እርምጃ አለመውሰድ ዋጋ እያስከፈለ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የአማራም ሆነ የኦሮሞ አምባገነን አያስፈልግም። ሁሉም እኩል ነው። ስልጣን የሚገኘው በምርጫ ነው። አማራ የኦሮሞን ጡት ቆርጧል፤ እንዲህ አድርጓል መባል የለበትም። የሚያዋጣን እውነት ድርጊቱ ተፈፅሞ ከሆነ ለታሪክ መተው ይሻላል። ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጥናት አጥንተው ኦሮሞ ጎንደርን በሙቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት መግዛቱን ፅፈዋል። እንደውም ጎንደርን ለ700 ዓመት የኦሮሞ ገዢ አስተዳድሮታል ብለው አጥንተዋል። የኋላውን አስቦ አማራዎች እንዲህ ገዝተውናል ማለት ኋላቀርነት ነው።

ቀደም ሲል የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቦ ለማ መገርሳ የኋላውን እያሰብን ወደ ፊት መሄድ አንችልም ብለዋል። ያለፈው አልፏል። ያለፈውን ለታሪክ መተው ይኖርብናል። አሁን ያለው አዲስ ሥርዓት እና አዲስ መንግሥት ነው። አዲስ ሥርዓት በመገናኛ ብዙኃን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር የሚተረጎም መሆን አለበት። ከታች እስከላይ መዋቅሩን ማስተካከል በሁለት ቢላዋ የሚበሉ ጉቦኞች ካሉ መንግሥት ማፅዳት አለበት። የሕወሓት ርዝራዥ የሆኑ ችግር እንዲፈጠር፤ ሰላም እንዳይኖር፤ መንግሥት እርምጃ እንዳይወስድ የሚያደርጉ በሙሉ በትክክል ተጣርተው ከስልጣን መውረድ አለባቸው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ትክክለኛውን ሰው ለትክክለኛ ቦታ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የሰው ልጅ በበሽታ፣ በጎርፍ እና በመሬት መንቀጥቀጥ በተፈጥሮ አደጋ ሊሞት ይችላል። ከዛ ውጪ ማንም ሰው ያለሕግ ውሳኔ ሰውን መግደል አይችልም። ይህ መንግሥትን መናቅ ነው።ለዚህ ደግሞ የተናቀው መንግሥት ስልጣን ላይ መሆኑን ማሳየት አለበት። በእርግጥ በመነፅር ወይም በኤክስሬ አጣርቶ አይቶ መሾም አይቻልም። ማንም ሌባ ሊሰበሰብ ይችላል።

ሰላምን የሚያደፈርስ አውቆ የሚያጠፋን

**አሁንም የትግራይን ሕዝብ እየበደሉ ያሉት ራሳቸው ወያኔዎች ናቸው። ታዲያ ስራሳቸው በቅርብ ሳለው ሕዝባቸው እንኳ ካልሆኑት ከወያኔዎች ጋር እንዴት ተባብሮ ሕዝብን ያጠቃል?**

ከመምከር እና ከመገሰፅም ያለፈ እርምጃ ያስፈልጋል።ሰላም ከገበያ የሚገዛ አይደለም። በተለይ የተከበረውን የሰውን ልጅ ነፍስ ያጠፋ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት አለበት። እንደመንግሥቱ ኃይለማሪያም እና በ1997 በመለስ ዜናዊ ጊዜ በአደባባይ ሰው እንደተገደለው ያለፍርድ መግደል ትክክል አይደለም። ነገር ግን ሕግ ማስከበር ደግሞ የግድ ነው። ብዙ ምሁራን ተናግረዋል። ይህች አገር ያጣችው እና የምትሞተው በምግብ እጦት ሳይሆን በፍትሕ እጦት ነው። መንግሥት ይህንን ሕገወጥነትን ለማስቆም ይሠራል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ሆነ ብሎ ሰው የገደለ ፤ መግደሉ ከተረጋገጠ ሊተው እና ምሕረት ሊደረግለት አይገባም።

**አዲስ ዘመን፡- የፍትሕ መስፈን የሚጠቅመው ማንን ነው? ፍትሕ አለመስፈኑስ የሚጎዳው ማንን ነው?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** ፍትሕ! ሰው የገደለ ሰው የሕዝብም የመንግሥትም ጠላት ነው። የሶስት ቀን ሕፃን መግደል የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው? ይህንን የፈፀመ ሰው እርምጃ ካልተወሰደበት ምንም ዋጋ የለውም። ፍትሕ የለም። የጦር ሜዳ ውጊያ ሌላ ነገር ነው። እንዲህ አይነት ድርጊት መፈፀም ጦርነት አይደለም። ሽፍታነት፣ ጨካኝነት እና አረመኔነት ነው። እነዚህን ማስተማር ያስፈልጋል። እርምጃ እየተወሰደ ነው እየተባለ ነው። ነገር ግን መቀጣጫ እንዲሆኑ ማስቻል ያስፈልጋል። ያለበለዚያ ይኸው ተግባር ይቀጥላል። እንኳን የሰው ልጅ አውሬ በጫካ ውስጥ በሰላም የመኖር ስልጣን አለው። እኛ ሰዎች እንዴት እንገዳደላለን? መንግሥት በፍፁም እነዚህን መማር የለበትም።

የኦሮሞን ባህል ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኦሮሞ ኩሩ ሕዝብ ነው። እነአብዲሳ አጋ፣ እነጀነራል ደስታ ገመዳ፣ እነኃይሌ ፊዳን የመሳሰሉ ጀግኖች የወጡት ከኦሮሞ ነው። ኦነግ ሸኔ የእነዚህን ጀግኖች ስም የሚያጠፋ ነው። እነሌንጮ ለታም ሆነ ዲማ ነገዎ ለ47 ዓመታት ሲታገሉ የነበረውን ትተው ፓርላማ ገብተዋል። ሰላም ካልሰፈነ ተጎጂው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መንግስትም ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ሸኔ ዓላማው እና ፍላጎቱ ምንድን ነው? ከሕወሓት ጋር ግንኙነት እንዳለውም ይታወቃል? የኦሮሞ ሕዝብን እና ወያኔን እንዴት ያዩታል?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** የሚገርመው ይሔ ነው።ኦሮሞ ነኝ የሚል እንዴት ከወያኔ ጋር ይገናኛል? ወያኔ እኮ ለ27 ዓመታት ከገዛ በኋላ ያለእኛ ኢትዮጵያን መምራት የሚችል የለም ብሎ በንቀት የሸፈተ ነው።ሸኔዎች ውስጥ የተማሩም አሉ ይባላል።እንዴት ከወያኔ ጋር እንደተባበሩ ግልፅ አይደለም።ድሮም ቢሆን ኦነግን ያባረረው ወያኔ ነው።በወያኔ የሥልጣን ዘመን ብዙ ቄሮዎች መስዋዕት ሆነዋል።እየተሳደዱ ተገድለዋል።ከወያኔ ጋር መተባበር ወያኔን ለመጣል የታገሉትን እና ብዙ ዋጋ የከፈሉትን የብዙ ቄሮዎችን ደም ደመከልብ ማድረግ ነው።

ወያኔ «ኦሮሞም አማራም ኢትዮጵያን መግዛት የለበትም፤ መግዛት ያለብን እኛ ብቻ ነን» ብሎ ጦርነት አወጀ።የትግራይ ሕዝብ መቼ ተበደለ? የለውጡ መንግሥት በጀት አልከለከለም።እንደውም ከጦርነቱ በፊት ለማቋቋሚያ በሚል ለሌሎች ክልሎች ያልተሰጠውን ለትግራይ ማቋቋሚያ በማለት ወደ ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር ተበጅቶላቸው ነበር። ይህ መንግሥት ምንም አላጠፋም። አሁንም የትግራይን ሕዝብ እየበደሉ ያሉት ራሳቸው ወያኔዎች ናቸው። ታዲያ ለራሳቸው በቅርብ ላለው ሕዝባቸው እንኳ ካልሆኑት ከወያኔዎች ጋር እንዴት ተባብሮ ሕዝብን ያጠቃል? በውጪ ያሉ የሸኔም ሆኖ የወያኔ ደጋፊዎች ድጋፋቸውን ማቆም አለባቸው በእነዚህ ሽፍቶች ኢትዮጵያ እየተጎዳች ነው።

ጦርነትን ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ አይቻለሁ። ጦርነት ለማንም አይጠቅምም። እንኳ ኢትዮጵያን ለመሰለች ደሃ አገር ቀርቶ እነዩክሬንና ራሽያዎች ምን እንደሆኑ እየታየ ነው። ዩክሬንን አውቃታለሁ። ነገር ግን እንዲህ ጦርነት አፈራርሷት እንዳልነበረች ሆና ስመለከት በጣም አዝናለሁ። ትምህርት ቤቱም ሆስፒታሉም መሠረተ ልማቱ በሙሉ ወድሟል። አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ጦርነት እንዲኖር ማድረግ በእውነት ትልቅ ጥፋት ነው። በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነት ግፍ መፈፀም ኦሮሞን ማዋረድ ነው። በእርግጥ ሸኔ ኦሮሞን አይወክልም። ኦሮሞ ጨዋ እና ኩሩ ሕዝብ ነው። አማራም ጨዋ ሕዝብ ነው። ተዘዋውሬ አይቻለሁ። ባህርዳር ኮረም መቶ ሺህ ጦር እመራ ነበር። አማራም ሆነ ኦሮሞ ሁለቱም ክብራቸውን የሚጠብቁ ጀግኖች ናቸው።

ከአሁን በኋላ መብቃት አለበት። በየትኛውም ቦታ ያጠፋ በሸኔ ስም ሌላው ሳይጎዳ በመዋቅር ውስጥ ያሉትም ቢሆኑ ተጣርተው እርምጃ መወሰድ አለበት። ከዚህ በላይ መተላለቅ አያስፈልግም፤ ኢሕአፓ እና መኢሶን እየተባለ ተተኪ የሌላቸው ትልልቅ ምሑራኖች አልቀዋል።እዚህ ላይ የኦሮሞ ምሑራን መንቃት አለባቸው። ከዚህ በላይ ጦርነት መኖር የለበትም ። በደርግም ጊዜ ጦርነት መፍትሔ አልሆነም። አንበሳ እንኳን ካልተራበ ሰው አይበላም፤ በእጁ ይዳብሳል። የሰው ልጅ በሰላም መኖር ሲችል፤ ችግርም ካለ ተነጋግሮ መፍታት እየተቻለ ጥጋበኛ ጉርባ ሆኖ ሰው ከተፈጀ ትዕግስትም ወሰን አለው። ሃይ መባል አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት አጥፊዎችን ለማስታገስ ምን ዓይነት መንገድን መከተል ይገባል?**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** አንድ የፀጥታ አስከባሪ ካለበት ቦታ ላይ በአስር ኪሎ ሜትር ቅኝት እያደረገ መቆጣጠር ይኖርበታል። የኦሮሚያ አጠቃላይ አስተዳደር ከመንግሥት ጋር ተሰልፎ እነዚህን ኦሮሞን የሚያዋርዱ ሽፍቶችን ማስቆም ይኖርበታል። ሸኔን ማጥፋት ይቻላል። ዝም ከተባለ አደጋ አለው። አልሸባብ ቤተመንግሥት ድረስ እየሔደ መድፍ ይተኩሳል። እነዚህ እዛ ድረስ እንዳይዘልቁ ቀድሞ መቆጣጠር ያስፈልጋል። ሳይንሱን መከላከያ ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡

ሕዝብን ማስረዳት መንገር፤ ከዛ መከታተል በመጨረሻም ማጥፋት የግድ ነው። ሽፍታ፣ ወንበዴ እና አመፅኛ የሚወጣው ከሕዝብ ነው። መልሶ የሚሸሸገው ሕዝብ ውስጥ ነው። ስለዚህ ለሕዝቡ ወንበዴን ማገዝ እንደሌለበት በደንብ ማስረዳት ያስፈልጋል። ሽፍታ ሰው ነው። ጫካ ውስጥ ቅጠል በልቶ አይኖርም። ወደ ሕዝብ ተጠግቶ መብላቱ አይቀርም። ስለዚህ ለሕዝቡ ወንበዴን አትደግፍ ጠቁም ከተባለ በትክክል ማጥፋት ይቻላል።

በየክልሉ የቀድሞ ሠራዊት አለ። መንግሥት የቀድሞ ሠራዊትን በሚገባ መጠቀም አለበት። ሠራዊቱ የተማረ እና ዲሲፕሊን ያለው ነው። በእነርሱ በኩል መቆጣጠርም ይቻላል። እኛ ዕድሜያችን አልፏል። ነገር ግን ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በታች የሆኑ ከ100 ሺህ ያላነሱ የቀድሞ ሠራዊት አባላት አሉ። ደርግ ብሔራዊ ውትድርናን አሰልጥኖናል። በየክልሉም የሰለጠኑ አሉ። የአሁኑ ጀግናው የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊትም አለ። 140ሺህ ሆኖ እስከ አፍንጫው ታጥቆ የመጣውን ወንበዴ በ50ሺህ ሠራዊት ማባረር ችሏል። ስለዚህ ጋምቤላም ሆነ ኦሮሚያ ላይ ጥፋት የሚፈፅሙትን የቀድሞ ሠራዊት አባላትንም ሆነ አዲሱን ሠራዊት በመጠቀም መቆጣጠር ይቻላል። ዕድሜያቸው ያለፉት ሳይቀሩ ሳይንሱን ማስተማር ይችላሉ። ዋናው ጉዳይ እነርሱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ መሆን ነው።

ሌላው በአማራ ክልልም በኩል በፋኖ ስም የሚነግዱ ሕገ ወጦች ስለመኖራቸው እየተነገረ ነው። እነርሱም ላይ ቢሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። በተጨባጭ ሆን ብሎ ሰው የገደለ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። ያለበለዚያ ስርዓት አልበኝነት ይቀጥላል። መከላከያን ሁሉም ቦታ ላይ ማሠማራት ስለማይቻል ቢያንስ በየክልሉ ያለውን የቀድሞ ሠራዊት የውጊያ ልምድ እና ዲስፕሊን ያለው በመሆኑ ሰፈር ጠባቂ ሊያደርጉት ይችላሉ። መደበኛው ሠራዊት ግዳጅ ሲሔድ የቀድሞ ሠራዊት ደግሞ አካባቢውን በመጠበቅ ያግዛል። ይህ ከሆነ ያሉ ችግሮችን ማስወገድ ይቻላል። ፋኖም ሆነ ቄሮ ልዩ ኃይልም ሆነ ሌላ ሥርዓትን አክብረው የመንግሥትን ትዕዛዝ ተቀብለው ለሀገር ሰላም ከቆሙ ሁሉም ነገር ከባድ አይሆንም የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡**

**ብርጋዴር ጀኔራል ዋስይሁን፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ለሦስተኛ ዙር የሥልጣን ዘመን እያሰቡ መሆኑን ተናገሩ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በአመራራቸው ላይ ከፍተኛ ትችት በሚሰነዘርበት በአሁኑ ወቅት ለሦስተኛ ጊዜ የሥልጣን ዘመን «በንቃት እያሰቡ» እንደሆነ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሁለተኛ ጊዜ ሙሉ የሥልጣን ዘመናቸው ዘመን እስከ አውሮፓውያኑ 2028 ወይም 2029 ድረስ ማገልገል ይፈልጋሉ ወይ ተብለው ተጠይቀው ነበር።

«በአሁኑ ወቅት ለሦስተኛው የሥልጣን ዘመን እና ከዚያ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በንቃት እያሰብኩ ነው፤ ነገር ግን በወቅቱ ስደርስበት እገመግመዋለሁ» ሲሉ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

ሆኖም አንድ የፓርላማ አባል ሕጎቹ ተቀይረው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሥልጣን እንዲወርዱ ሌላ የመተማመን ድምፅ (ኮንፊደንስ ቮት) እንዲደረግባቸው ጠይቀዋል።

በኮመንዌልዝ የመሪዎች ስብሰባ ላይ ሰሞኑን በተገኙበት በሩዋንዳ፣ ኪጋሊ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየታቸውን እንዲያብራሩ ተጠይቀው «ለሦስተኛ ጊዜ በአውሮፓውያኑ 2030ዎቹ አጋማሽ ላይ እያሰብኩ ነው» ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ጆንሰን ፓርቲያቸውን ወደ ቀጣዩ ምርጫ እንደሚመሩ ገልፀው፣ በመላ አገሪቱ ያለውን መበላለጥ ለማስተካከል እቅዳቸውን ወደፊት መቀጠል እንደሚፈልጉ ተናግረዋል። መንግሥታቸው ይህንን እርምጃ «ደረጃ ማሳደግ» ብሎ ነው የሚጠራው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን እኩልነት ማምጣት ጊዜ እንደሚወስድ ቢያምኑም፣ በሁለቱ ፓርላማዎች በሚደረገው ከፍተኛ ማሻሻያ ሊሳካ እንደሚችልም አክለዋል።

«እኔን እዚህ ቦታ ላይ እርሱኝ። ይህች አገር፣ እንግሊዝ ምን ማድረግ እንደምትችል እና የት እንዳለች አስቡ» ሲሉ ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

«መንግሥትን ለመለወጥ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ወስደናል። ለምሳሌም የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት እና የሕግ ሥርዓታችንን፣ ድንበሮችን የምናስተዳድርበትን መንገድ፣ ኢኮኖሚያችንን እና የምንሠራቸውን ሁሉንም ዓይነት ሥራዎች በተለየ መንገድ እየሠራን ነው» ብለዋል።

«እንዲሁም በአገር ደረጃ አንድ ታላቅ ፕሮጀክት ጀምረናል። ይህም አንድነት እና ደረጃን ከፍ የሚያደርግ ነው። በዚህ ፕሮጀክት አስደናቂነት በልበ ሙሉነት አምናለሁ» ብለዋል።



## ሩሲያ የኒዩክሌር አቅም ያላቸው ሚሳኤሎችን ለመተኮስ የሚያስችል ሥርዓት ለቤላሩስ እንደምትሰጥ አስታወቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ በሚቀጥሉት ወራት የኒዩክሌር አቅም ያላቸውን አጭር ርቀት ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን ለመተኮስ የሚያስችል ሥርዓት ወደቤላሩስ እንደምትልክ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን አስታወቁ።

ፕሬዚዳንቱ እንዳሉት ኢስካንድር- ኤም የተባለው ሥርዓት የባልስቲክ እና የክሩዝ ሚሳኤሎችን መተኮስ የሚችል ሲሆን እስከ 500 ኪሎ ሜትር መሸፈን ይችላል።

ባለፈው የካቲት ወር ላይ በሩሲያና ዩክሬን መካከል የተጀመረውን ጦርነት ተከትሎ በሩሲያና በምዕራባውያኑ መካከል ያለው ውጥረት ጨምሯል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ፑቲን ስለ ኒዩክሌር የጦር መሣሪያዎች ብዙ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ይህንን ንግግራቸውን አንዳንዶች የምዕራብ አገራት ጣልቃ እንዳይገቡ ለማስጠንቀቅ ያለመ ነው ብለውታል።

ፑቲን የሩሲያ የወደብ ከተማ በሆነችው ሴንት ፒተርስበርግ ንግግር ባደረጉበት ወቅት ከቤላሩስ ፕሬዚዳንት ሉካሸንኮ ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፣ ሩሲያ የቤላሩስ ኤስዩ-25 የጦር አውሮፕላኖች የኒዩክሌር የጦር መሣሪያዎችን መያዝ እንዲችሉ ለማድረግ ትረዳለች ብለዋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን ከአቻቸው የቤላሩሱ ፕሬዚዳንት አሌክሳንደር ሉካሸንኮ ጋር ባደረጉትና ቅዳሜ ዕለት በቴሌቪዥን በተላለፈው ስብሰባ ላይ «ወስነናል። በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ለቤላሩስ ኢስካንደር- ኤም የተባለውን የሚሳኤል መተኮሻ ሥርዓት እናስረክባለን» ብለዋል።

መሣሪያዎቹን የማስረከብ ዝርዝር ሂደቱን የሁለቱ አገራት መከላከያ ሚኒስትሮች በኩል እንደሚሠሩም ፕሬዚዳንቱ አክለዋል።

ኢስካንደር ሚሳኤሎች የኔቶ አባል በሆኑት ሊቱኒያ እና ፖላንድ መካከል በምትገኘው የሩሲያ ባልቲክ ባህር ዳርቻዋ ካሊኒንግራድ ተሰማርተዋል።

ሁለቱ ፕሬዚዳንቶች የሉትዌኒያ አንዳንድ ዕቃዎች ወደ ካሊኒንግራድ እንዳይጓዙ ለመከላከል ባደረገችው ውሳኔ ላይ የተወያዩ ሲሆን እርምጃው ሞስኮን አስቆጥቷል።

የቤላሩሱ ፕሬዚዳንትም የሉትዌኒያ እርምጃ «የጦርነት አዋጅ እና ተቀባይነት የሌለው ነው» ብለዋል።

ሉትዌኒያ ግን እርምጃዋ ተፅዕኖ የሚያሳድረው ለወትሮው በወደቡ ከሚተላለፉ የሩሲያ ምርቶች መካከል አንድ በመቶ በሚሆነው ላይ ነው ስትል ሩሲያ ካሊኒንግራድ አግዳለች ስትል ያቀረበችውን ክስ አጣጥላለች።

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ዘይኑ ጀማል የሰሌዳ ቁጥር 2 ኦሮ 10017 ሊብሬ የጠፋ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/10/14 ዓ.ም አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የመኪናው ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ሊብሬ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ባሥልጣን**

### አማራ ክልል

በከሳሽ፡- ጉብና ተፈሪ በተከሣሾች፡- 1ኛ ጉብረስላሴ አሻግሬ 2ኛ. አማረች ሞላ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ ተከሣሾች በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተከሰሳችሁ እና ሐምሌ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ቀጠሮ ይዞ የሚጠባበቅ መሆኑን አውቃችሁ በተጠቀሰው ቀን አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እንድትቀርቡ በዚህ የጥሪ ማስታወቂያ መሰረት የማትቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌላችሁበት ታይቶ ተገቢው የሚወሰን መሆኑን እንድታውቁት ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት**

በይ/ባይ፡- ዐ/ህግ መ/ሰጪ፡- ወርቅየ ምስጋናው መካከል ስላለው የከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክስ ጉዳይ በቀጠሮው እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ጊዜ ቢታዘዝም በትእዛዙ ሊገኙና ሊቀርቡ ባለመቻልዎ ጥሪው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን አውቀው ለሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ለሆነው ቀነ ቀጠሮ በአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እንዲያውቁት የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት አዟል።

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጎንደር ምድብ ችሎት**

በከሣሾች፡- 1ኛ/ ጌታቸው ጌትየ
2ኛ/ አቶ ይድነቃቸው አበባው
በተከሳሾች፡- 1ኛ/ ወ/ ሂሩት አድማሱ
2ኛ/ ህብረት ኢንሹራንስ

ጣ/ገብ------ኦሮሚያ ኢንሹራንስ መካከል ስላለው የጉዳት ካሳ ክርክር ጉዳይ ከሣሾች 1ኛ/ ጌታቸው ጌትየ 2ኛ/ አቶ ይድነቃቸው አበባው በቀጠሮው እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ቢተላለፍም ሊገኙ/ሊቀርቡ/ ባለመቻላቸው በማስታወቂያ ጥሪ እንዲደረግ ትዕዛዝ የተሰጠ ስለሆነ ለቀጠሮው ለሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም አብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት እንድትቀርቡ የማትቀርቡ ከሆነ ግን ጉዳዩ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እንዲያውቁት የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ጎንደር ምድብ ችሎት አዟል

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጎንደር ምድብ ችሎት**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ወ/ሮ መሰረት ታደሰ እና በተከሳሽ አቶ በየነ ኢቲቻ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ27/10/2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ፡- ወ/ሮ የሺወርቅ ድረስ እና በተከሳሽ፡- አቶ መሀመድ ሙስጠፋ ጨመዳ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ ለ04/11/2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 3፡30 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በአመልካች ፡- ወ/ሮ ቢቷልሄም ወርቁ ታምሬ በተጠሪ፡- አቶ ኢትባረክ ሐጎስ አበራ ተጠሪ በአድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ስላልቻሉ ለ28/10/2014 ዓ.ም 3፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 7ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በአመልካች፡- ወ/ሮ ስላስ ሀይሉ እና ተጠሪ፡- አቶ ታፈረ ዘውገ ከ10/9/1991 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ተጠሪ አቶ ታፈረ ዘውገ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ23/10/2014 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከ የ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት ከጠዋቱ 4፡00 እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ፡- አመልካች ወ/ሮ ብርቱካን ተሾመ በቀለ እና ተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ሳይመን ለሚኬኚ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ27/10/2014ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች፡- የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ደረጀ አለማየሁ መካከል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢንቨስትመንት ምድብ 5ኛ ባ/ኢንሹራንስ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ22/10/2014 ዓ.ም 3፡40 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም አቶ መሀመድ ሀይደር አብዶ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-51879 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNC3CA714392 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*120317044967 የሊብሬ ቁጥር 010215 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ12/10/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል።

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ቢኒያም ቦጋለ ብዛዬ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-75545 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JT1E0EE9000219504 ሞዴል EE90L-AEKDEW የሞተር ቁጥር Unreadable የሊብሬ ቁጥር 390206 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ15/10/2014 ዓ.ም አመልክተዋል።

የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገኛል የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ደጀኔ ለማ ኩባ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-50579 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3GMS004082278 ሞዴል 330-30H የሞተር ቁጥር 8210.22*511-227414* የሊብሬ ቁጥር 0203946 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/10/2014 ዓ.ም. አመልክተዋል።

ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ስፖርት

## መከላከያ ከመጪው ዓመት ጀምሮ በቀድሞ ስሙ ‹መቻል› ሊጠራ ነው

**ቦጋለ አበበ**

ባለፈው ዓመት ከከፍተኛ ሊግ ወደ ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር መመለሱን ያረጋገጠው መከላከያ እግር ኳስ ክለብ የዘንድሮውን የውድድር ዓመት በሊጉ መቆየቱን ለማረጋገጥ ሁለት ጨዋታዎች ይቀሩታል፡፡ ያም ሆኖ የመከላከያ ስፖርት ክለብ በመጪው ዓመት ላይ በቀድሞ የመቻል ስሙ ሊጠራ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በኢትዮጵያ የስፖርት ታሪክ ውስጥ በስመ ገናናነቱ የሚታወቀው እና የበርካታ ዋንጫዎችና የሜዳሊያዎች ባለቤት በመሆን አኩሪ ስም ያለው መከላከያ በቀድሞ ጊዜ ስሙ በሚጠራበት መቻል ስያሜውን ከመጪው ዓመት ጀምሮ የሚያገኝ እና የሚጠራበት ይሆናል፡፡ ይኸው ክለብ በ81 ዓመት የምስረታ ታሪኩም የመቻል ስፖርት ክለብ በሚል የደጋፊዎች ማህበር አቋቁሞ የእውቅና ፈቃድንም ከማኅበራት ማደራጃ ሚኒስትር ሊወስድም እንደቻለ ተነግሯል።

የመከላከያ ስፖርት ክለብ በኢትዮጵያ የስፖርት ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ማለትም ከአስር በላይ በሚደርሱ ስፖርቶች በመሳተፍ እና ውጤታማም በመሆን ብዙ ዝናን ያተረፈ ሲሆን፣ በርካታ ስፖርተኞችንም ለሀገሪቱ ማፍራት ችሏል። ይሄ ክለብ ከሚወዳደርባቸው የስፖርት ዘርፎች መካከል በተለይም በእግር ኳሱ በጣም የሚታወቅ ሲሆን በቀድሞው ጊዜም እንደ እነ አረፋይኔ፣ ቡታ አስምሮምን፣ መርሻ ሚደቅሳን፣ በሀብቱ ገብረማሪያምን፣ ሙሉዓለም እጅጉን፣ ሙሉጌታ ብርሃኔን፣ ደረጀ በላይን፣ ክፍሌ ቦልተናን፣በሀይሉን፣ ማቲያስ ሀብተማሪያምን፣ ታሪኩ መንጀታን፣ አለምሰገድ አንቼን፣ በለጠ ወዳጆን ማፍራት ችሏል፡፡ ከ1996 ዓም በኋላ ደግሞ እስከዚህ ዘመን ድረስ እየተጫወቱ ያሉ እና ኳስን መጫወት ያቆሙ በርካታ ተጨዋቾችንም ለእውቅና ሊያበቃ ችሏል።



**መከላከያ ስፖርት ክለብ ዓመታትን ባስቆጠረ ጉዞው በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች አገርን ያኮሩ ስፖርተኞችን በማፍራት ቀዳሚ ነው፣**

መከላከያ በቀድሞ ጊዜ አሁን የስም ለውጥ በማድረግ የመቻል ስፖርት ክለብ ተብሎ ሊጠራ እንደተዘጋጀ ሁሉ ምድር ጦርም ተብሎ ይጠራ የነበረ ሲሆን፣ ክለቡ በእግር ኳሱ በተለይም ደግሞ ከ1970ዎቹ አጋማሽ አንስቶ በነበረው ዝናና ውጤታማነት ከደጋፊዎቹ ይሰጠው የነበረው ድጋፍ እና ማበረታታትም ታሪክ የማይረሳው እንደሆነ ይታወቃል፡፡

መከላከያ ወደ ሜዳ ያኔ ሲገባ መጠሪያ ስሙ ምድር ጦርም ተብሎ ይጠራ የነበረ ሲሆን "ይናዳል ገደሉ፤ ጦሩ መጣ ሲሉ" የሚለውና "አማሬሳ ሆ! አማሬሳ ሆ! ጦሩ ነመኛታ" የሚሉት ዜማዎችም የሚታወሱለት ናቸው።

የመከላከያ ስፖርት ክለብ በአዲሱ የውድድር ዘመን መቻል በሚል ስያሜው መጠሪያውን በሚያደርግበት ወቅትም አስቀድሞ የቀድሞ የቡድኑ ደጋፊዎች ማኅበራቸውን ከአቋቋሙ በኋላ የሥራ ክፍፍል ያደረጉ ሲሆን፣ አቶ ኤልያስ አብርሃምን በሊቀመንበርነት፣ ወይዘሮ መንበረ ቀፀላን በምክትል ሊቀመንበርነት፣ አቶ ዳንኤል ኃይለ ሚካኤልን በዋና ጸሐፊነት፣ እንደዚሁም ደግሞ አቶ ተስፋዬ ታደሰን በሕዝብ ግንኙነት በመምረጥ እና በአጠቃላይም 15 የሚደርሱ አባላቶችንም በማካተት የሥራ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ መዘጋጀታቸው ታውቋል፡፡

የመከላከያ ስፖርት ክለብ መቻል በሚል የቀድሞ ስሙ በመጪው ዓመት ላይ ሊጠራ ዝግጁ በሆነበት በአሁኑ ሰዓት እንደ ቡድኑ የቀድሞ ቀንደኛ ደጋፊዋ መንበረ ቀፀላ ሁሉ በበፊቱ ጊዜ ቡድኑን አብራት ባማረ ሁኔታ ትደግፍ የነበረችው ፍሬሕይወትም ከምትኖርበት አሜሪካ በመምጣት የቡድኑ የደጋፊዎች የክብር አባል እንድትሆን የተደረገች ሲሆን፣ በምትኖርበት የሰሜን አሜሪካ ላስቬጋስ ከተማም የቡድኑ ተጠሪ ልትሆን ችላለች። ሌላዋ ደጋፊ ገነት አየለም በፈረንሳይ ሀገር የመቻል ስፖርት ክለብ ተጠሪ እና በእዚህ የተመሠረተው የክለቡ የደጋፊዎች ማኅበር የክብር አባልም ለመሆን በቅታለች።

የመከላከያ በአዲሱ ስያሜው የመቻል ስፖርት ክለብ የደጋፊዎች ማኅበር የአባልነት ምዝገባውን በቅርቡ እንደሚጀምር የተነገረ ሲሆን የማኅበሩ ጽሕፈት ቤትም ለጊዜው ጃንሜዳ በሚገኘው የክለቡ ካምፕ እንደሆነም ተነግሯል፡፡

የመከላከያ ስፖርት ክለብ ምስረታ ጣሊያን ከአገር በወጣ ማግስት በ1938 ዓ.ም ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የክለቦች ምስረታ ታሪክ ከቀዳሚዎቹ የሚመደብም ነው። ዓመታትን ባስቆጠረ ጉዞውም በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ሀገርን ያኮሩ ስፖርተኞችን በማፍራት ቀዳሚ ነው። ክለቡ በአትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ቮሊቦል እና እጅ ኳስ ስፖርቶች በክለብ ደረጃ ንቁ ተሳትፎ ከማድረግም በላይ ለብሔራዊ ቡድን ተመራጭ ተጫዋቾችና በማፍራትም ጭምር ምስጉን ክለብ ነው። በአጠቃላይ ስፖርተኛው 500 የሚደርሱ ሲሆን፤ ተቋሙ በጃንሜዳ አካባቢ ባለው ካምፕም መቀመጫቸውን አድርጓዋል። ክለቡ ስፖርተኞችን ከታዳጊ ጀምሮ ወደ ዋናው ቡድን የሚያሳድግ በመሆኑ ለምልመላ ይረዳው ዘንድም በየዓመቱ በተለያዩ አካባቢዎች የራሱን ውድድር ያካሂዳል። በአትሌቲክስ ስፖርትም ሠራዊቱን ለመቀላቀል ፈቃደኛ ለሆኑት እንዲሁም ከሠራዊቱ መካከል ለስፖርቱ ብቁ የሆኑትን ክለቡ አቅፎ ይይዛል።

የአትሌቲክስ ስፖርት የክለቡ መነሻ ነው፤ በኦሊምፒክ መድረክ ባዶ እግሩን በመሮጥ «ብቻውን ሮምን ወረራት» የተባለለት አበበ ቢቂላ ደግሞ የክለቡ ፍሬ ነው። ባሻዬ ፈለቀ፣ ማሞ ወልዴ፣ ምሩጽ ይፍጠር፣ እሸቱ ቱራ፣ መሃመድ ከድር እና ሃዲስ አበበም የውትድርናው ዓለም ለኢትዮጵያ ያበረከታቸው ቀደምት እንቁዎች ናቸው። አሁንም ኢብርሂም ጄይላን፣ ኢማና መርጋ፣ ሱሌ ኡቱራ፣ የማነ ጸጋዬ፣ አልማዝ አያና፣ ሙክታር እድሪስ፣ እቴነሽ ዲሮ፣ አስካለ ቲከሳ፣.... ከበርካቶቹ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡


## በጉምሩክ ኮሚሽን የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የተተዉና የተወረሱ ዕቃዎች ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 40/2014

በጉምሩክ ኮሚሽን የሐዋሳ ጉምሩክ ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት በሀዋሳ ማዕከላዊ መጋዘን የተተዉና ተወርሰው የሚገኙ የተለያዩ ያገለገሉ ሞተር ሣይክሎች የመዋቢያና የንፅህና መጠበቂያዎች ባሉበት ሁኔታ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም በጨረታው መወዳደር የሚፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. ተሽከርካሪዎች ላይ መወዳደር የሚፈልግ ተጫራች ማንኛውም እድሜው ከ18 አመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ መወዳደር ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ተጫራች የጨረታውን ሰነድ በጨረታ ማስታወቂያው ላይ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ጠዋት ከ2:00 እስከ 6:00፣ ከሰዓት ከ7:00 እስከ 11፡00 ሰዓት ቅዳሜ ከ 2፡00 እስከ-6፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል በቅ/ጽ/ቤቱ ከገቢ ሂሳብና ዋስትና አስተዳደር ቢሮ መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም የግልፅ ጨረታ ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% (አምስት በመቶ) በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተመሰከረለትን C.P.O፣ የጨረታ ሰነድ እና አጠቃላይ መረጃዎችን ጨረታው ከመከፈቱ በፊት በጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
4. ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሰነዱን በመግዛት እስከ 7ኛው (ሰባተኛው) ቀን ድረስ የንብረቶቹን ናሙና በመደበኛ የስራ ሰዓት በሀዋሳ ማዕከላዊ መጋዘን ማየት የሚችሉ ሲሆን ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን በ8ኛው (ስምንተኛው) ቀን የግልፅ ጨረታ ጠዋት 4፡00 ሰዓት የጨረታ ሳጥኑ ታሽጎ በ4፡05 ሰዓት ማዕከላዊ መጋዘን ይካሄዳል:: ነገር ግን ጨረታው በበዓል (እሁድ) ቀን የሚውል ከሆነ ጨረታው የሚካሄደው በተመሳሳይ ሰዓት በሚቀጥለው የስራ ቀናት ይሆናል፡፡
5. ማንኛውም የግልጽ ጨረታ ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዞ በቀረበው ቅጽ ላይ ተጫራቹ ያቀረበው ዋጋ በሚለው ርዕስ ስር በተሰጠው ክፍት ቦታ ከነቫት እና ያለቫት በሚል በጨረታ ሰነዱ ግልፅ በሆነ መልክ በመሙላት በታሸገ ኤንቨሎፕ ወይም ፖስታ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከዚህ ሰነድ ውጪ በሌላ ሰነድ ተሞልቶ የሚቀርብን ዋጋ ቅ/ጽ/ቤቱ ለመቀበል አይገደድም::
6. ማንኛውም የግልፅ ጨረታ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ በጨረታ ሰነድ ላይ የሰጠውን ዋጋና መግለጫ መለወጥ እና ማሻሻል አይችልም፡፡
7. ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ሂደት ተጠናቆ ቅ/ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡
8. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ እራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይችልም፡፡
9. በጨረታው ለተሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት CPO በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊው ያስያዘው ዋስትና ግን ከሽያጭ ጋር የሚታሰብለት ይሆናል፡፡
10. ተጫራቾች ዕቃውን ሳያዩ ዋጋ ቢሰጡና ችግር ቢፈጠር ኮሚሽኑ ተጠያቂ አይሆንም::
11. ለጨረታው የቀረበው ዕቃ ሽያጭ የሚፈፀመው ባለበት ሁኔታ ነው::
12. አሸናፊ ተጫራቾች ማሸነፋቸው በውስጥ ማስታወቂያ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5(አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፈበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃዎችን ማንሳት ይኖርባቸዋል ይህንን ባያደርጉ ጨረታው ተሠርዞ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡
13. ቅ/ጽ/ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ የስልክ ቁጥር -0462125396**

**በጉምሩክ ኮሚሽን የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት**